# - 9 -

# ክርስቲያን ምን ማድረግ ይገባዋል?

## ሉቃስ 10

በምዕራፍ 10 ውስጥ የሚገኙት ሦስት ትእይንቶች የእያንዳንዱን አማኝ ክርስቲያን ባለ ሦስት ገጽታ አገልግሎት በማብራራት፥ «ክርስቲያን ምን ማድረግ ይገባዋል?» ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣሉ።

በመጀመሪያ ደረጃ፥ በዚህ ዓለም እርሱን ለመወከል የተላክን የጌታ አምባሳደሮች ነን (ቁጥር 1-24)። እንዲሁም፥ በክርስቶስ ስም ምሕረትን ለማሳየት አጋጣሚዎችን የምንፈልግ ባልንጀሮች ነን (ቁጥር 25-37)። ይህም ሆኖ፥ ከአገልግሎታችን ሁሉ ለክርስቶስ የመገዛታችን ጉዳይ ማዕከላዊውን ስፍራ ይይዛል፤ ስለሆነም ቃሉን ለመስማትና ከእርሱ ጋር ለማሳለፍ ጊዜ በመውሰድ የምናመልከው ልንሆን ይገባል (ቁጥር 38-42)።

በእርሻ ቦታ፥ በመንገድ ላይ ወይም በቤት ውስጥ ብንሆን፥ ታላቁ ጥቅማችንና ከፍተኛው ደስታችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ነው።

## 1. ጌታን የምንወክል አምባሳደሮች (10፡1-24)።

ይህ ክስተት ከአሥራ ሁለቱ መላክ ጋር ሊደናገር አይገባም (9፡1-11፤ ማቴ. 10)። በተሰጡት ትእዛዛት መካከል ተመሳሳይነት ቢኖርም፥ ሁለቱም ቡድኖች የተላኩት መሠረታዊ አንድነት ያለውን ተግባር ለማከናወን በአንዱ ጌታ በመሆኑ ልንገረም አይገባም። አሥራ ሁለቱ ያገለገሉት በገሊላ ሲሆን፥ እነዚህ ግን የተላኩት ወደ ይሁዳ ነበር፤ በዚህ ምዕራፍ የምናገኛቸው ሰዎች ሐዋርያት ተብለው አልተጠሩም። እነርሱ በስማቸው ያልታወቁ የኢየሱስ ተከታዮች ነበሩ።

ሉቃስ ብቻ ይህንን ክስተት የመዘገበው ለምንድን ነው? ጌታስ ላልጠፉ ቁጥር ሰባ ሰዎችን የመረጠው ለምንድን ነው? (አንዳንዶች ሰባ ሁለት ሲሉ፥ የምንባብ መረጃውም "textual evidence") የሚደግፋቸው ይመስላል።) አሥራ ሁለቱ ከአሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆችና ከአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ጋር እንደተዛመዱ ሁሉ፥ ምናልባትም ሰባዎቹም በዘፍጥረት 10 ከተዘረዘሩት ሰባዎቹ የሕዝብ ወገኖች ጋር ይዛመዱ ይሆናል። የሉቃስ አጽንኦት በወንጌል መልእክት

ዓለም-አቀፋዊነት ላይ በመሆኑ ይህንን ክስተት ለማከል በመንፈስ ቅዱስ እንደተመራ አድርጎ መውሰዱ ተገቢ ይመስላል።

ማብራሪያ (ቁጥር 1-12)። እነዚህ ሰዎች «ሐዋርያት» ተብለው ባይጠሩም፥ ጌታ ለሚሰጠው «ተልእኮ የተላኩ [ኤፖስተሎ] ነበሩ። ስለሆነም፥ በትክክል የንጉሡ አምባሳደሮች ነበሩ። በእርሱ መላክ ብቻ ሳይሆን፥ ለመምጫው ጥርጊያ መንገድ ያዘጋጁ ዘንድ ከፊቱም ተልከዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ ጥሪያቸው የከበረ ነበር።

ጥሪው አስቸጋሪ ነበር (ቁጥር 2)። ብዙ አጋሮች እያሉ እንኳ የመከር ሥራ አስቸጋሪ ነው! እነዚህ ሰዎች ግን ለአጨዳው እገዛ ከሚያደርጉላቸው ጥቂት ሰዎች ጋር ወደ ሰፊ የእርሻ ማሳ ተልከው ነበር። ቀላል ሥራ እንዲሰጣቸው ከመጸለይ ይልቅ ብዙ ሠራተኞች እንዲጨመሩ መጸለይ ያስፈልጋቸው ነበር! እኛም ዛሬ የእነርሱን ዓይነት ጸሎት ልንጸልይ ይገባል። (ተጨማሪ ሠራተኞች እንዲመጡ የሚጸልዩት ታዛቢዎች ሳይሆኑ ሠራተኞች መሆናቸውን ልብ በል! እጅግ ብዙ ክርስቲያኖች ራሳቸው ሊያደርጉ ያልፈለጉትን ሥራ ሌሎች ያከናውኑ ዘንድ ይጸልያሉ።)

ጥሪያቸው አደገኛ ነበር። የጠላትን ክልል ሲወሩ (ቁጥር 17) «በተኩላዎች መካከል እንደሚገኙ በጎች» ነበሩ (ቁጥር 3)። ይህም ሆኖ፥ በጌታ ላይ እስከተደገፉበት ጊዜ ድረስ ውጊያውን ያሸንፉ ነበር። ብዙ ጊዜ ቫንስ ሐቭነር ለአድማጮቻቸው፥ «ኢየሱስ ክርስቶስን በትጋት የሚከተል ማንም ቢሆን የዲያብሎስ የዒላማ ማነጣጠሪያ ይሆናል! ግን አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን አባላት ሰይጣንን ስለማያስቸግሩ እርሱ ችግር አይፈጥርባቸውም» ይሉ ነበር።

ሥራውን ለማከናወን እምነትና ራስን መግዛት ያስፈልጋቸው ነበር (ቁጥር 4-8)። ሥራው የሚያስቸኩል በመሆኑ፥ ጌታ በተጨማሪ ሸክሞች እንዲደከሙ ወይም ረዥም ሰላምታ እየተለዋወጡ በመንገድ ላይ እንዲዘገዩ ፈጽሞ አልፈለገም። እግዚአብሔር ቤቶችንና ምግብ እንደሚያዘጋጅላቸው ማመን ሲኖርባቸው፥ ሌሎች በእንግድነት ሲቀበሉአቸው ማረፍ አይገባቸውም ነበር። ይኸውም፥ እነዚህ ሰዎች ለጌታ በመሥራት ላይ በመሆናቸውና ለሚገቡባቸው ቤቶች በረከት እያመጡ ስለሆነ ነው! «ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋልና» (ቁጥር 7፤ 1ኛ ቆሮ. 9፡14 እና 1ኛ ጢሞ. 5፡18 ተመልከት)።

ለታመመው ጤንነትን፥ በአጋንንት ለተያዘው ነፃ መውጣትን፥ ከደኅንነት ርቀው ለጠፉት የደኅንነትን መልካም የምሥራች

የሚያመጡ የሰላም አምባሳደሮች ነበሩ። እንደ ቀድሞው የኢያሱ ሠራዊት፥ መጀመሪያ ለከተሞች ሰላምን ያውጃሉ። የሰላምን ስጦታ አልቀበልም የምትል ከተማ ካለች፥ ፍርድን መረጠች ማለት ነው (ዘዳግ. 20፡10–18)። እግዚአብሔር የሚልካቸውን አምባሳደሮች አለመቀበል አደገኛ ነገር ነው።

ኢየሱስ ለሐዋርያቱ (9፡1) እና ለሰባዎቹ የሰጠው ልዩ ኃይል ዛሬም የእኛ እንደሆነ ማሰብ የለብንም። እነዚህ ሁለት የስብከት አገልግሎቶች በጣም ልዩ ሲሆኑ፥ እግዚአብሔርም እነዚህኑ አገልግሎቶች በእኛ ዘመን እንደሚደግም ቃል አልገባም። ጌታችን ለእኛ የሰጠው ተልእኮ የተአምራትን አደራረግ ሳይሆን፥ የወንጌሉን መሰበክ ያጠናክራል (ማቴ. 28፡19–20፤ ሉቃ. 24፡46–49)።

<u>ክህደት</u> (ቁጥር 13–16)። ይህ ከእግዚአብሔር ልጅ አፍ ሊወጣ የማይገባ ጠንካራ የቃላት አጠቃቀም ቢመስልም፥ ችል ለማለት ወይም ለማቃለል ልንሞክር አንደፍርም። በእግዚአብሔር የተፈረደባቸውን ሦስት ጥንታዊ ከተሞች ማለትም ሰዶም (ዘፍጥ. 19)፥ ጢሮስና ሲዶናን (ሕዝ. 26–28፤ ኢሳ. 23) ከጠቀሰ በኋላ፥ በዘመኑ የነበሩትን ሦስት ከተሞች ኮራዚን፥ ቤተ ሳይዳና ቅፍርናሆምን ለማስጠንቀቅ ተጠቅሞባቸዋል። እነዚህ ሦስቱ ከተሞች ከጥንቶቹ የበለጠ ዕድሎች ስለነበሩ፥ ኃላፊነታቸውም ያንኑ ያህል የከበደ ነበር። ሰዶም፥ ጢሮስና ሲዶና ከወደሙ፥ ኮራዚን፥ ቤተ ሳይዳና ቅፍርናሆምስ እንዴት ያመልጣሉ?

የክርስቶስን አምባሳደሮች መስማት ማለት እርሱን መስማት ማለት ነው፤ የእርሱን ወኪሎች መናቅ ደግሞ እርሱን መናቅ ነው። «አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ» (ዮሐ. 20፡21፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡18–21 ተመልከት)። አንድ አገር አንድን አምባሳደር የሚያስተናግደው አምባሳደሩ የሚወክለውን አገር በሚያስተናግድበት መንገድ ነው። የዚህን እውነት አስገራሚ ማብራሪያ ለመረዳት 2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 10ን አንብብ።

<u>ሐሤት</u> (17፡24)። በዚህ ስፍራ ባለ ሦስት ገጽታ ደስታ ይታያል፤ የአገልግሎት ደስታ (ቁጥር 17፡19)፥ የደኅንነት ደስታ (ቁጥር 20) እና የሉዓላዊነት ደስታ (ቁጥር 21–24)።

ሰባዎቹ ድሎቻቸውን ለኢየሱስ ለመንገር ሲመለሱ የነበራቸውን ደስታ ልንረዳ እንችላለን። እንዲፈውሱ፥ አጋንንትን እንዲያስወጡና ቃሉን እንዲሰብኩ ኃይልና ሥልጣን የሰጣቸው ሲሆን፥ በተሳካ ሁኔታ

ፈጽመውታል። በከፍተኛ ደስታቸው ውስጥ «በስምህ» በማለት ለእግዚአብሔር ክብሩን ለመስጠት ተጠንቅቀዋል።

እነርሱ ከከተማ ከተማ አንዳንድ ድሎችን ቢመለከቱም፥ ኢየሱስ ግን እነዚህን ድሎች የተመለከተው ሰይጣንን ያሸነፈውና ከዙፋኑ ያፈናቀለው ጦርነት አካል አድርጎ ነበር (ኢሳ. 14:4-23፤ ዮሐ. 12:31-32፤ ራእ. 12:8-9 ተመልከት)። አማኞች እንደመሆናችን፥ በራሳችን ደካሞች ነን፤ ዳሩ ግን በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታን ልንሆን እንችላለን (ኤፌ. 6:ከ10 ጀምሮ)። በዓይናችን ፊት ምንም ያህል አላስፈላጊ ቢመስልም፥ እያንዳንዱ ድል ለጌታ አስፈላጊ ነው። ሰይጣን ኢየሱስ በመጨረሻው ወደ እሳት ባሕር እስኪያወርደው ድረስ ወደ ፍርድ አይመጣም (ራእ. 20:10)፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ ግን ዛሬ የክርስቶስን የጐልጐታ ድል በእምነት ሊያውጅ ይችላል (ቈላ. 2:15)።

ጠላት ግን ተስፋ ቆርጦ ቁጭ አይልም! ሰይጣን የክርስቶስን ባሪያዎች ማጥቃቱና ሊያጠፋቸውም መጣሩ የማይቀር ነው። ጌታችን በቁጥር 19 የማበረታቻ ቃላት ያከለው ለዚህ ነው። በዚህ ጊዜ የስብከት አገልግሎት በማብቃቱ ሥልጣናቸው እንዳልተለያቸውና «የቀደመውን እባብ» ያለ ፍርሃት ሊረግጡ እንደሚችሉ አረጋግጦላቸዋል (ራእ. 12:9፤ ዘፍጥ. 3:15)።

ጌታችን በድላቸው ብቻ መደሰታቸውን እንዳይቀጥሉና ዳሩ ግን ስሞቻቸው በሰማይ ስለ ተጻፉ እንዲደሰቱ አስጠንቅቆአቸዋል። (ግሡ ስሞቻቸው እንደተጻፉና ተጽፈውም እንደሚኖሩ ያመለክታል። ይህ የዋስትና አሳብ ነው። ራእይ 20:12-15፤ ፊልጵስዮስ 4:3 ተመልከት።) የፈጸሙአቸው ተአምራት ግሩም ድንቅ ቢሆኑም፥ ከሁሉ የበለጠ ተአምር ከደኅንነት ርቆ የጠፋው ሰው ደኅንነት ማግኘት ነው። «ተጻፉ» የሚለው ቃል በግሪኩ «ሕጋዊና የጠበቀ ጽሑፍ (ማኅተም)» የሚል ፍች አለው። ይህ ውርስን፥ የጋብቻ ሰነድን፥ ወይም የሰላም ውልንና የዜግነት ምዝገባን ለመፈረም ያገለግል የነበረ ቃል ነው።

ይህም ሆኖ፥ ከሁሉም የሚልቀው ደስታችን የሚመጣው ከአገልግሎታችን ወይም ከደኅንነታችን ሳይሆን፥ ለሰማያዊ አባታችን ሉዓላዊ ፈቃድ ከመገዛታችን ነው፤ ይህ የአገልግሎትም ሆነ የደኅንነት መሠረት ነውና ። በዚህ ስፍራ ከእግዚአብሔር አብ ፈቃድ የተነሣ እግዚአብሔር ወልድ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሐሴት ሲያደርግ እንመለከታለን። «አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ» [መዝ. (40):8]።

ኢየሱስ የተደሰተው ኃጢአተኞች ለእግዚአብሔር እውነት በመታወራቸው አይደለም፤ እግዚአብሔር ማንም እንዲጠፋ የሚፈልግ አይደለምና (2ኛ ጴጥ. 3፡9)። የተደሰተው የዚያ እውነት ግንዛቤ በተፈጥሮአዊ ችሎታዎች ወይም በትምህርት ላይ ባለመደገፉ ነው። ይህማ ቢሆን ኖሮ ብዙዎቹ ሰዎች ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጭ ይሆኑ ነበር። አሥራ ሁለቱና ሰባው በሚያገለግሉበት ጊዜ «ጠቢባንና የተማሩ ሰዎች» የእግዚአብሔርን እውነትና ጸጋ ለመቀበል ራሳቸውን ዝቅ ሲያደርጉ አልተመለከቱም፤ ይልቁንም «ተራ ሰዎች» ቃሉን ሲያምኑ ተመለከቱ (7፡29-30፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡26-29)። ኃጢአተኞች ከፍ ከፍ ከመደረጋቸው በፊት ራሳቸውን ዝቅ ዝቅ እንዲያደርጉ እግዚአብሔር በሉዓላዊ ፈቃዱ ወስኖአል (1ኛ ጴጥ. 5፡6፤ ያዕ. 4፡6)።

እንደ እውነቱ ከሆነ የክርስቶስ አምባሳደሮች የታደሉ ሕዝቦች ነበሩ። በብሉይ ኪዳን ዘመን ታላላቅ ቅዱሳን ለመስማትና ለማየት ተመኝተው ያላገኙአቸውን ነገሮች ለማየትና ለመስማት ችለዋል። መሢሑ በሥራ ላይ ሲሆን፥ እነርሱም የሥራው አካል ነበሩ።

## 2. ጌታን የምንመስል ባልንጀሮች (10፡25-37)።

የአይሁድ የሃይማኖት መምህራን (ረቢዎች) የሥነ-መለኮት ጉዳዮችን በአደባባይ ላይ እንደሚወያዩ የሚጠበቅ ሲሆን፥ ይህ ጸሐፊ (ሕግ አዋቂ) የጠየቀው ጥያቄ ብዙውን ጊዜ አይሁዶች የሚከራከሩበት ነበር። ሕግ አዋቂው ጥያቄውን ያነሣው ጌታችንን ለማጥመድ መሆኑ ከፉ ዓላማ እንደነበረው ቢጠቁምም፥ ጥያቄው ግን ጥሩ ነበር።

ጌታችን ሰውዬውን ወደ ኋላ ወደ ሕግ መለሰው፤ ይህንንም ያደረገው ሕግ ስለሚያድነን ሳይሆን፥ ዳኑ ግን ሕጉ መዳን እንደሚያስፈልገን ስለሚያሳየን ነው። ያለ ኃጢአት ወቀሳ ምንም ዓይነት እውነተኛ መለወጥ ስለማይኖር፥ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ለመውቀስ በሕግ ይጠቀማል (ሮሜ. 3፡20)።

ጸሐፊው ትክክለኛ መልስ ቢሰጥም፥ ጉዳዩን ከግል ሕይወቱ ጋር አገናዝቦ ለእግዚአብሔርም ሆነ ለባልንጀራው ፍቅር እንዳልነበረው አምኖ ሊቀበል አይችልም ነበር። ስለሆነም፥ በእግዚአብሔር ምሕረት ሥር ራሱን ጥሎ እንደ መጽደቅ (18፡9-14)፥ ራሱን ማጽደቅና በአዘቅት ውስጥ መንሸራሸርን መረጠ። ያረጀ የሙግት ዘዴ ይጠቀም ጀመር፤ «ምን ለማለት እንደፈለግህ ግልጽ አድርገልኝ! ‹ባልንጀራ› ስትል ምን ማለትህ ነው? ባልንጀራዬስ ማን ነው?»

ኢየሱስ ይህ ታሪክ ምሳሌ እንደሆነ ስላልተናገረ፥ የተፈጸመ ነገር ሊሆን ይችላል። ለኢየሱስ አይሁዶችን እንደ ክፉዎችና ሰማርያውያንን እንደ መልካሞች በታሪክ መግለጥ አንድም አደገኛ አልያም ራስን ለሽንፈት መዳረግ ነበር። ሁሉም፥ «ይህ አንተ የፈጠርኸው ነው! እንዲህ ዓይነት ነገር በፍጹም እንደማይደርስ ሁላችንም እናውቃለን!» ለማለት ይችሉ ነበር። ስለሆነም፥ ሕግ አዋቂውን ጨምሮ ከአድማጮቹ አንዳንዶቹ እንዲህ ዓይነት ነገር በትክክል እንደተፈጸመ ሳያውቁ አይቀሩም። በሁለቱም በኩል ዘገባው እውነት ነው።

ስለ ማንኛውም ምሳሌ፥ በተለይም ስለዚህኛው፥ ልንፈጽም የምንችለው ከሁሉም የከፋ ስህተት ተምሳሌታዊ ትርጉም በመስጠት «ይኼ ይኼን፥ ያ ደግሞ ያንን ይወክላል» ማለት ነው። በዚህ ዓይነት አጉል አተረጓጎም ተጐጂው በሞትና በሕይወት (በሥጋ ሕያው፥ በመንፈስ ሙት) መካከል የሚገኘውና በምስኪንነት በሕይወት ጐዳና ላይ የተጣለው ኃጢአተኛ ይሆናል። ካህኑና ሌዋዊው ሕግንና መሥዋዕቶችን ይወክላሉ፤ ሁለቱም ታዲያ ኃጢአተኛውን ለማዳን የማይችሉ ናቸው።

ሰውዬውን የሚያድነው፥ ለዕዳው የሚከፍልለትና ዳግም ለመመለስ ቃል የሚገባው ሰማርያዊ ክርስቶስ ነው። የእንግዶቹ ማደሪያ ስፍራ ለአማኞች እንክብካቤ የሚያደረግበትን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሲያመለክት፥ «ሁለቱ ዲናሮች» ሁለቱን ሥርዓቶች ማለትም ጥምቀትንና ቅዱስ ቊርባንን ያሳያሉ። መጽሐፍ ቅዱስን በዚህ መልኩ የምትተረጉም ከሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ደስ የሚያሰኝህን የፈለግኸውን አቅጣጫ ይዞ እንዲሄድ ልታደርግ ትችላለህ፤ ይህም ሲሆን እግዚአብሔር እንድታገኛቸው የሚፈልጋቸውን መልእክቶች እንደምታጣ ጥርጥር የለውም።

ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ የሚያደርሰው መንገድ በእውነት አደገኛ ነበር። የመቅደስ አገልጋዮች አዘውትረው ስለሚመላለሱበት አይሁዶች ወይም ሮማውያን መንገዱን ሰላማዊ ለማድረግ እንደጣሩ ልታስብ ትችላለህ። ዳሩ ግን ጉርብትናን ከማሻሻል ይልቅ ሃይማኖታዊ ወግ መያዙ ይበልጥባቸው ነበር።

ብዙዎቻችን ሌዋዊውና ካህኑን የተጐዳውን ሰውዬ ለመርዳት ያልፈለጉባቸው ምክንያቶች እንዳሉአቸው ልንከራከር እንችላለን። (እኛም ራሳችን እንዲሁ አድርገን ይሆናል!) ካህኑ ሳምንቱን ሁሉ በመቅደሱ ውስጥ ጌታን ሲያገለግል በመቆየቱ ወደ ቤቱ ለመሄድ ቸኩሎ ነበር። ምናልባትም ወንበዴዎቹ በአካባቢው ተሸሽገው

የተጐዳውን ሰውዬ እንደ መጥለፊያ ወጥመድ ይጠቀሙበት ይሆናል። እርሱ ለምን ይርዳው? የሰውየውም መጐዳት የእርሱ ጥፋት አይደለም። በመንገዱ ብዙ ሰዎች ይተላለፉ ስለነበር፥ ሌላ ሰው መጥቶ ሊረዳው ይችላል ሲል አሰበ። ካህኑ ሰውየውን ለሌዋዊ ትቶ ሲሄድ፥ ሌዋዊውም ካህኑ ያደረገውን ነገር ደገመ– ምንም ሊያደርግለት አልፈለገም! የሃይማኖታዊው ሰው መጥፎ ምሳሌነት ኃይሉ እንዲህ ነው።

ኢየሱስ የሰማርያዊውን ሰውዬ ደግነት በማሳየት የአይሁዶችን ትጥቅ አስፈትቶአል፤ ምክንያቱም አይሁዶችና ሰማርያውያን ጠላቶች ነበሩና (ዮሐ. 4፡9፤8፡48)። የገዛ ወገኖቹ በሆኑት አይሁዶች የተገለለውን አይሁዳዊ የሚረዳው ሰማርያዊ እንጂ የሰማርያን ሰው የሚረዳ አይሁዳዊ አልነበረም። ሰማርያዊው የሚጠሉትን በመውደዱ ሕይወቱን በአደጋ ላይ ከመጣሉም በላይ ገንዘቡንም (ለሠራተኛው የሁለት ቀን ደመወዝ) ከሰረ፤ እስከምናውቀው ድረስ ለዚህ ተግባሩ የተደረገለት ይፋዊ ሽልማት ወይም ክብር አልነበረም።

ሰማርያዊው ያደረገው ነገር «ምሕረትን ማሳየት» (ቁጥር 37) ምን እንደሆነ የበለጠ እንድንረዳ ከማገዙም በላይ የኢየሱስ ክርስቶስንም አገልግሎት ያብራራልናል። ሰማርያዊው የአንግዳውን ሰው ጉድለቶች ለመሙላት ርኅራኄ አደረገለት። ዕቅዶቹን ተመልሶ የሚያስተካከለበትና በችግር ላይ ያለውን «ጠላት» ለመርዳት ገንዘቡን የሚከፍልበት አስተውሎታዊ ምክንያት ባይኖረውም፥ ምሕረት የማመኻኛ ምክንያቶችን እንደማይፈልግ ተገነዘበ። የሕግ አዋቂ እንደመሆኑ ጸሐፊው እግዚአብሔር ሕዝቡ ለእንግዶችና ለጠላቶቻቸው ሳይቀር ምሕረትን እንዲያሳዩ እንደሚፈልግ በትክክል ያውቅ ነበር (ዘሌ. 19፡33–34፤ ዘዳ. 23፡4–5፤ ሚክ. 6፡8)።

ኢየሱስ እንዴት በጥበብ ዞር ዞሮ የሕግ አዋቂውን አሳብ እንደ ገለበጠበት ልብ በል። ከኃላፊነት ለመሸሽ ሲል ሕግ አዋቂው «ባልንጀራዬ ማን ነው?» ሲል ጠይቋል። ኢየሱስ ግን፥ «ከእነዚህ ከሦስቱ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ባልንጀራው የሆነው የትኛው ይመስልሃል?» ሲል ጠየቀው። ዋናው ጥያቄ፥ «ለማን ባልንጀራ ልሆነው እችላለሁ?» የሚል ሲሆን፥ ይህ ከመልከዓምድር፥ ከዜግነት፥ ወይም ከዘር ሐረግ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም። ሰዎች በሚፈልጉን ስፍራ ሁሉ ባልንጀሮቻቸው ልንሆንና እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ምሕረትን ልናሳይ እንችላለን።

ሕግ አዋቂው «ባልንጀራ»ን በአጠቃላይ መልኩ ለማንሣት ቢፈልግም፥ ኢየሱስ ግን በችግር ውስጥ ያለውን አንድ ሰው

እንዲመለከት አስገደደው። ስለ ረቂቅ አሳቦች እየተወያዩ ተጨባጭ ችግሮችን ለማስተካከል እገዛ አለማድረጉ ቀላል ነገር ነው። «ረሃብ» እና «የሥራ ዕድሎች» በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ልንወያይና የተራበን ቤተሰብ ለመመገብ ወይም አንድ ሰው ሥራ እንዲያገኝ ለመርዳት ግላዊ እገዛ ላናደርግ እንችላለን።

ሕግ አዋቂው ጉዳዩን ለማወሳሰብና የፍልስፍና ገጽታ ለመስጠት ቢፈልግም፥ ኢየሱስ ግን ቀላልና ተግባራዊ አድርጎታል። ኢየሱስ ጉዳዩን ከግዴታ ወደ ፍቅር፥ ከክርክር ወደ ተግባር አሸጋገረው። በርግጥ ጌታችን ውይይቶችን ወይም ክርክሮችን እየኮነነ አልነበረም፤ ዳሩ ግን እነዚህን ነገሮች ለማመኻኘት በመጠቀም ምንም ነገር ሳንፈጽም እንዳንቀር ያስጠነቅቀናል። ድርጊት ፈጻሚ ኮሚቴዎች ሁልጊዜም ለተግባር የተሰጡ አይደሉም።

ከምወዳቸው የዲ. ኤል. ሙዲ ታሪኮች አንዱ ይህንን ነጥብ ጥሩ አድርጎ ያብራራዋል። ሚስተር ሙዲ በኢንዲያናፖሊስ አንድ ጉባኤ በመካፈል ላይ ሳሉ፥ ዘማሪ አይራ ሳንኪ አንድ ምሽት በሆነ የመንገድ ጥግ ላይ በአሥራ ሁለት ሰዓት ላይ እንዲገናኛቸው ይጠይቁታል። ሳንኪ በደረሰ ጊዜ ሚስተር ሙዲ በአንድ ሳጥን ላይ ከተቱትና መዝሙር እንዲዘምር ጠየቁት፤ ወዲያውም ሕዝብ ተሰበሰበ። ሙዲ አጭር ንግግር በማድረግ ሕዝቡ የሙዚቃ ዝግጅቶች ወደሚቀርቡበት ስፍራ አብርአቸው እንዲሄድ ጋበዙ። ብዙም ሳይቆይ የመሰብሰቢያ አዳራሹ ሞላ። ወንጌላዊውም ሙዲ መንፈሳዊ ረሃብ ላጠቃቸው ሰዎች ስብከት አቀረቡ።

የጉባኤው አባላት በሚገቡበት ጊዜ ሙዲ ስብከታቸውን አቆሙና፥ «አሁን የጉባኤው ተሳታፊ አባላት ‹ሕዝብን እንዴት እንድረስ?› በሚለው ጥያቄ ላይ ስለሚወያዩ ማቆም አለብን» አሉ። ማለፊያ ድል!

ይህንን ክፍል ስናነብ ምናልባት ለሌላው ሰው እንክብካቤ ማድረግ እጅግ ከባድ ዋጋ እንዳስከፈለን ልናስብ እንችላለን፤ ይህን አለማድረጉ ግን የበለጠ ከባድ ዋጋ እንዳለው ነው። ሰማርያዊው ተጎጂውን በመንከባከቡ ከከሰረው ይልቅ ካህኑና ሌዋዊው ችላ ብለው በማለፋቸው የከሰሩት ይበልጣል። መልካም መጋቢዎችና የተሻሉ ሰዎች ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ነገር ዕድላቸውንም አጥተዋል። በመጥፎው ዓለም ውስጥ መልካም ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ሲችሉ እነርሱ ግን ተቃራኒውን ለማሳደር መረጡ። የሰማርያዊው አንዲት የምሕረት ተግባር በዓለም ሁሉ የመሥዋዕትነትን አገልግሎት አነቃቃች። ከቶውንም የዚህ ዓይነቱ አገልግሎት እንደ ባከነ አትቁጠር።

እግዚአብሔር በክርስቶስ ስም የሚካሄድ ማንኛውም የፍቅር አገልግሎት እንዳይባክን ይቆጣጠራል።

ሁሉም የሚወሰነው በአመለካከትህ ነው። ይህ መንገደኛ አይሁዳዊ ለሌቦች የዝርፊያ ዒላማ በመሆኑ አጠቁት። ለካህኑና ለሌዋዊው ደግሞ አስቸጋሪ በመሆኑ ገለል ብለው አለፉት። ለሰማርያዊው ግን ሊረዳና ሊወደድ የሚገባ ባልንጀራ በመሆኑ እንክብካቤ አደረገለት። ኢየሱስ ለሕግ አዋቂው የተናገረውን ለእኛም ቃል በቃል ይደግምልናል፤ «ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ።»

## 3. ጌታን የምንሰማ አምላኪዎች (10፡38–42)።

አምልኮ በክርስትና ሕይወት የእኛነታችንና የተግባራችን እምብርት ነው። የወንጌሉን መልእክት ከደኅንነት ርቀው ለጠፉት ኃጢአተኞች በማድረስ ሥራ የሚበዛብን አምባሳደሮች መሆናችን አስፈላጊ ነገር ነው። እንዲሁም፥ የእግዚአብሔር ምሕረት የሚያስፈልጋቸውን ተጎጂና የተበዘበዙ ሕዝቦች በመርዳት ምሕረት አድራጊ ሰማርያውያን መሆናችንም ተገቢ ነው። ይህም ሆኖ፥ እንደሚገባን ክርስቶስን ከመወከላችን ወይም በፍቅር አገልግሎታችን እርሱን ከመምሰላችን በፊት፥ ከእርሱ ጋር ጊዜ ልናሳልፍና ከእርሱ ልንማር ይገባል። «ቅዱሳን ለመሆን ጊዜ መውሰድ» አለብን።

የቢታንያዋ ማርያም ሦስት ጊዜ በወንጌላት ውስጥ የተጠቀሰች ስትሆን፥ ሦስቱንም ጊዜ በተመሣሣይ ስፍራ በኢየሱስ እግር ሥር ነበረች። ከእግሩ ሥር ተቀምጣ ቃሉን ስትሰማ (10፡39)፥ ከእግሩ ሥር ወድቃ ኃዘኗን ስትገልጽ (ዮሐ. 11፡32)፥ እና ከእግሩ ሥር ተቀምጣ አምልኮዋን ስታቀርብ (ዮሐ. 12፡13) እንመለከታለን። በእነዚህ ሁሉ አጋጣሚዎች ሽታዎች መኖራቸውን ማጤኑ አስገራሚ ነገር ነው፤ በሉቃስ 10 የምግብ ሽታ፥ በዮሐንስ 11 የሞት ሽታ (ቁጥር 39)፥ በዮሐንስ 12 መልካም የሽቶ መዓዛ ነበር።

አንድ ክርስቲያን ምርጫ ሊያደርግ እንደሚገባ ሁሉ ማርያምና ማርታ ብዙውን ጊዜ ተነጻጽረው ይቀርባሉ፤ ይኸውም እንደ ማርታ ሊሠራ ወይስ እንደ ማርያም ሊያመልክ እንደሚገባው ነው። በመሠረቱ ባሕርይና ስጦታዎቻችን የተለያዩ ናቸው፤ ይህ ግን የክርስቲያን ሕይወት የፈለጉትን የሚመርጡበት እንደሆነ አያመለክትም። ቻርልስ ዌስሊ ከመዝሙሮቹ በአንዱ ይህንን በግሩም ሁኔታ አስቀምጦታል።

ዛሬም ይኺ ነው ምርጫዬ፥

የጌታዬን ትእዛዝ ተቀብዬ፥

መሥራት ማገልገሌ እንደ ማርታ፥

እንደ ማርያም ፊቱን ማየት በደስታ።

ይህ ጌታ እያንዳንዳችን በአምልኮአችን የማርያምን አርአያነት እንድንከተልና በሥራችን ደግሞ ማርታን እንድንመስል እንደሚፈልግ የሚያመለክት ይመስላል። ሁለቱንም ሚዛናዊ አድርገው የሚይዙ ብፁዓን ናቸው።

የማርታን ሁኔታ ተመልከት። ኢየሱስን ወደ ቤቷ ተቀበለችውና የማይፈልገውን ማለፊያ ምግብ ስታሰናዳ ችላ አለችው። በመሠረቱ ምግብ አስፈላጊ ነገር ነው፤ ዳሩ ግን ከክርስቶስ ጋር የምናደርገው ነገር ለክርስቶስ ከምናደርገው እጅግ የበለጠ ጠቀሜታ አለው። አሁንም ይህ አንዱን ከሌላው የምናማርጥበት ሳይሆን በሚዛናዊነት የምንጠቀምበት ነው። ማርያም በማዕድ ቤቱ የሚደርሳትን ሥራ ከጨረሰች በኋላ፥ የጌታን ትምህርት «ለመመገብ» ሄደች። ማርያም ከማዕድ ቤቱ ወጥታ ከሄደች በኋላ ማርታ ብቻዋን እንደተተወች በማሰብ ማርያምም ሆነች ጌታ እንደማያስቡላት ትናገርና ታጉረመርም ጀመር።

ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ሳያደርጉ በፊት ለክርስቶስ ለመሥራት የመሞከርን ያህል የክርስትናን ሕይወት የሚጐዳ የባሰ ነገር የለም። «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና» (ዮሐ. 15፡5)። ማርያም ግን ከእርሷ የማይወሰደውን መልካም ነገር መረጠች። «በእንጀራ ብቻ» ልትኖር እንደማትችል ተረድታ ነበር (ማቴ. 4፡4)።

ሌሎችን ስንተችና ብዙ እንደሠራን በማሰብ ለራሳችን ስናዝን፥ የራሳችንን ሕይወት ለመመርመር ጊዜ ብንወስድ መልካም ነው። ምናልባትም በጥድፊያችን ሁሉ ጌታን ችል እያልን ይሆናል። የማርታ ችግር የሥራዋ መብዛት ሳይሆን፥ ሥራዋ አእምሮዋን እንዲያውክና ሰላምዋን እንዲወስድ ማድረጓ ነው። ሁለት ጌቶችን ለማገልገል እየሞከረች ነበር። ክርስቶስን ማገልገል ሕይወታችንን የሚያውከው ከሆነ፥ በአገልግሎታችን በኩል አንድ የከፋ ነገር አለ ማለት ነው።

ቁልፉ የነገሮችን ትክክለኛ ቅደም ተከተል መጠቀም ስለሆነ፤ መጀመሪያ ክርስቶስ ሊቀድም፥ ከዚያም ሌሎች፥ በመጨረሻም ራሳችን ልንከተል ይገባል። ቃሉን እንዲያካፍለን በመፍቀድ በየዕለቱ «በኢየሱስ እግር ሥር» ጊዜ ማሳለፋችን እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። የክርስትና ሕይወት ዋነኛው ስፍራ እግዚአብሔር ብቻ የሚመለከተው ክፍል ነው። በየዕለቱ ከክርስቶስ ጋር በግላችን የማንገናኝ ከሆነ ብዙም

ሳይቆይ እንደ ማርታ ተስፋ ቆርጠን እናቆማለን–በረከትን ሳይሆን ባዶነትን አጭደን!

በመጋቢነት አገልግሎቴ ብዙ ጊዜ ከባድ መንፈሳዊ ችግር ያጋጠማቸውን ሰዎች «ስለ ጽሞና ሕይወታችሁ ንገሩኝ» ስል ጠይቄአለሁ። የተለመደው መልስ ኃፍረት ያጠላበት እይታ፥ ራስን ዝቅ ማድረግና «ከብዙ ጊዜ በፊት መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብና መጸለይ አቁሜአለሁ» የሚል በዝግታ የሚገለጽ ኑዛዜ ነው። እንዲህ እየኖሩ ነው እንግዲህ ለምን መንፈሳዊ ችግር አጋጠመን የሚሉት!

እንደ ዮሐንስ 12፡1–2 አገላለጽ ማርታ ከገጠመኟ ትምህርት አግኝታለች ማለት ነው! ለኢየሱስ፥ ለአሥራ ሁለቱ፥ ለወንድሟና ለእህቷ ግብዣ አድርጋለችና– ለእነዚህ አሥራ አምስት ሰዎች የሚበቃ ምግብ ስታዘጋጅ አንድም የማጉረምረም ቃል አልወጣትም ነበር። ከኢየሱስ እግር ሥር መቀመጥን ስለተማረች፥ በልቧ የእግዚአብሔር ሰላም ነግሦ ነበር።

እኛ አምባሳደሮች፥ ባልንጀሮችና አምላኪዎች ሦስቱንም ነን። ከእነዚህ ሁሉ የሚበልጠው ደግሞ አምላኪዎች መሆናችን ነው።

የነገሮችን ሚዛን ጠብቀው የሚመላለሱ ብፁዓን ናቸው!

# – 10 –

# የሕይወትን ትምህርቶች መማር

## ሉቃስ 11

በምዕራፍ 11 የጌታችን ትምህርት የተሰጠው በጸሎት ስብሰባ፥ በተአምርና በእራት ግብዣ ነው። ኢየሱስ ለአራት አስፈላጊ ርእሰ–ጉዳዮች ትምህርቶችን ለመስጠት እነዚህን ጊዜያት ተጠቀመ፤ አራቱም ጉዳዮች ጸሎት፥ ሰይጣን፥ መንፈሳዊ በርና ግብዝነት ናቸው። ዛሬ እነዚህን ርእሰ–ጉዳዮች ተረድቶ ከራሳችን ሕይወት ጋር ማዛመድ አስፈላጊ ነው።

### 1. ጸሎት (11፥1–13)።

<u>የጸሎት ቀዳሚነት</u> (ቁጥር 1)። ብዙውን ጊዜ መጥምቁ ዮሐንስን የምናስታውሰው እንደ ነቢይና ሰማዕት ሲሆን፥ የጌታችን ደቀ መዛሙርት ግን እንደ ጸሎት ሰው አስታወሱት። ዮሐንስ ከመወለዱ በፊት «ተአምረኛ ሕፃን» ቢሆንም፥ ሳይወለድ በፊት በመንፈስ ቅዱስ ቢሞላ እንኳ መጸለይ አስፈለገው። መሢሑን ለእስራኤል የማስተዋወቅ ዕድል የነበረው ቢሆንም እንኳ መጸለይ አስፈለገው። ኢየሱስ ዮሐንስ ከነቢያት ሁሉ እንደሚበልጥ የተናገረለት ቢሆንም (7፥28) መጸለይ ያስፈልገው ነበር። ጸሎት እነዚህ አያሌ ዕድሎች ለነበሩት ሰው አስፈላጊ ከሆነ፥ እነዚህ ዕድሎች ለሌሉን ለእኛስ ምን ያህል ያስፈልገን ይሆን?

የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት የግድ መጸለይ ያስፈልጋቸው ነበር፤ የኢየሱስም ደቀ መዛሙርት እንዴት በተሻለ ሁኔታ ለመጸለይ እንደሚችሉ ለመማር ፈለጉ። የጠየቁት እንዴት መስበክ እንዳለባቸው ወይም ታላላቅ ምልክቶችን ማድረግ እንዲያስተምራቸው ሳይሆን፥ ጸሎትን እንዲያስተምራቸው ነበር። አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ከእርሱ ጋር ብንሆን ኖሮ የተሻልን ክርስቲያኖች እንድንሆን እናስባለን፤ ይኼ ግን የማይመስል ነው። ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ ጋር ቢሆኑም ብዙ ጊዜ ወድቀዋል። ተአምራት ለማድረግ ቢችሉም፥ እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው ሊማሩ ፈለጉ።

ይሁንና፥ ለጸሎት ቀዳሚነት ከሁሉም የሚበልጠው ነጥብ ጌታችን ተግቶ ይጸልይ የነበረ መሆኑ ነው። እስካሁን እንደተመለከትነው በጥምቀቱ ወቅት (3፥21)፥ አሥራ ሁለቱን ከመምረጡ ቀደም ብሎ (6፥12)፥ ሕዝቡ በተበራከተ ጊዜ (5፥16)፥ አሥራ ሁለቱን የእምነት

መግለጫ ከመጠየቁ በፊት (9፡18)፥ ብሎም መልኩ በተለወጠበት ጊዜ (9፡29) ሲጸልይ ተመልክተናል። ደቀ መዛሙርቱ ብዙ ጊዜ ብቻውን ሲጸልይ ስለሚያዩ (ማር. 1፡35)፥ ይህንን መንፈሳዊ ኃይልና ጥበብ ከእርሱ ሊማሩ ፈለጉ።

ፍጹም የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋው ወራት (ዕብ. 5፡7) በጸሎት ላይ ለመደገፍ ከተገደደ፥ እኔና አንተስ ምን ያህል አብልጠን ልንጸልይ ይገባል! ውጤታማ ጸሎት ጉድለትን ሁሉ የሚሞላና፥ ለማንኛውም ችግር መፍትሔ የሚያስገኝ ነው።

<u>የጸሎት አመራር</u> (ቁጥር 2-4)። ይህንን ጸሎት «የጌታ ጸሎት» ብለን የምንጠራው ኢየሱስ ስለ ጸለየው ሳይሆን (የይቅርታ ጸሎት ማድረግ አያስፈልገውም ነበር)፥ ኢየሱስ ስላስተማረው ነው። ይህንን ጸሎት በእውነተኝነት ለጌታ ከተሰጠ የሚያምን ልብ እስከጸለይን ድረስ፥ በግልም ሆነ በጉባኤ በኅብረት መጸለዩ ስሕተት አይደለም። እነዚህን ቃላት በቃል እያነበቡ ከልብ አለመጸለዩ ቀላል ነው! ይህ ደግሞ በምንሰብከበትና በምንዘምርበትም ጊዜ ሊደርስ የሚችል ነገር ነው። ጥፋቱ እንግዲህ የራሳችን እንጂ የጸሎቱ አይደለም።

ይህም በግላችን ስንጸልይ እንዲመራን የተሰጠን «ምሳሌያዊ ጸሎት» ነው (ከማቴ. 6፡9-5 ተመሳሳይ አሳብ ተመልከት)። እውነተኛ ጸሎት እግዚአብሔርን «አባት» ብለን እንድንጠራው በሚያስችል መንፈሳዊ ዝምድና ላይ እንደሚመሠረት ያስተምረናል! ይህም ሊመጣ የሚችለው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው (ሮሜ. 8፡14-17፤ ገላ. 4፡1-7)።

በእውነተኛ ጸሎት ውስጥ ኃላፊነትም አለ፤ ይኸውም የእግዚአብሔርን መንግሥት ማክበርና የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም ነው (ቁጥር 2)። የጸሎት ዓላማ የሰውን ፈቃድ በሰማይ ላይ መፈጸም ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በምድር ላይ ማከናወን እንደሆነ የሚገልጸው አባባል እውነት ነው። ጸሎት የምንፈልገውን ነገር ለእግዚአብሔር በመናገር በምናገኘው ውጤት በራስ-ወዳድነት መደሰት አይደለም። ጸሎት ስሙ እንዲከብር፥ መንግሥቱ እንዲሰፋና እንዲጠናከር፥ ብሎም ፈቃዱ እንዲፈጸም የሚፈለገውን ተግባር ለማከናወን እንዲጠቀምብን እግዚአብሔርን መጠየቅ ነው። እግዚአብሔር ጸሎትን ሰምቶ እንዲመልስ ከፈለግን፥ በእነዚህ የበላይ አሳቦች ግላዊ ጥያቄዎችን ሁሉ መመርመር አለብን።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከውስጡ ስለምናገኝ ለእኛ ለክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ አስፈላጊ ነው። ከቶውንም ጸሎትንና

ቃሉን መነጣጠል የለብንም (ዮሐ. 15፡7)። በአገልግሎት ዘመኔ ክርስቲያኖች ነን የሚሉ ሰዎች እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ፥ «ስለ ጉዳዩ ጸልዩ እግዚአብሔርም ይሁን ብሎኛል» እያሉ የመከላከያ አሳብ ሲያቀርቡ ተመልክቻለሁ። ይህም ደኅንነትን ያላገኘ ሰው ያገባችውን ሴት (2ኛ ቆሮ. 6፡14–18)፥ ሚስቱ ካልሆነች ሴት ጋር የሚኖረውን ወንድ (1ኛ ተሰ. 4፡1–8)፥ እንዲሁም ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሳቱ እንደሆኑና እርሱ ብቻ እውነተኛ «መንፈሳዊ መረዳት» እንዳለው በመግለጽ የራሱን ቤተ ክርስቲያን የመሠረተውን ሰባኪ ይጨምራል (ፊልጵ. 2፡1–16)።

ከእግዚአብሔርና ከፈቃዱ ጋር ያለን ግንኙነት ከተስተካከለ በኋላ ጥያቄዎቻችንን ወደ እርሱ ልናቀርብ እንችላለን (ቁጥር 3–4)። ለዛሬም (የምንፈልገውን ሳይሆን) የሚያስፈልገንን እንዲሰጠን፥ ትናንት ለፈጸምነው በደል ይቅር እንዲለንና ወደፊትም ከእኛ ጋር ሆኖ እንዲመራን ልንጠይቀው እንችላለን። የሚያስፈልጉን ነገሮች ሁሉ በእነዚህ ሦስት ጥያቄዎች ውስጥ ሊጠቃለሉ ይችላሉ፤ እነዚህም ቁሳዊና ሥጋዊ ልግስና፥ ሥነ–ምግባራዊና መንፈሳዊ ፍጹምነትና መለኮታዊ ጥበቃና ምሪት ናቸው። በዚህ መንገድ የምንጸልይ ከሆነ፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ መጸለያችን ዋስትና ሊኖረን ይችላል።

<u>ሳያቋርጡ መጸለይ</u> (ቁጥር 5–8)። በዚህ ምሳሌ ኢየሱስ እግዚአብሔር እንደዚህ ነዝናዛ ጐረቤት እንደሆነ አልተናገረም። እንዲያውም ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት የዚህ ተገላቢጦሽ ነው። አንድ ራስ–ወዳድ ጐረቤት በድካም ቢዝልም እንኳ በመጨረሻ የሚነዘንዘውን ወዳጅ ጉድለቶች ካሟላ፥ አፍቃሪ ሰማያዊ አባትስ የውድ ልጆቹን ጉድለት እንደ ምን አብልጦ ያሟላ ይሆን!

ጸሎት በልጅነት («አባታችን ሆይ») ላይ እንጂ በወዳጅነት ላይ እንደማይመሠረት ቀደም ብለን ተመልክተናል። ነገር ግን፥ ኢየሱስ ሳያቋርጡ ስለ መጸለይ ለማብራራት ወዳጅነትን ተጠቅሟል። እግዚአብሔር አብ ከቶውንም እንደዚህኛው ጐረቤት አይደለም፤ ይኸውም እርሱ በፍጹም አይተኛም በጭራሽ ትዕግሥቱም አያልቅም ወይም አይናደድም። ዳሩ ግን ሁልጊዜም ለጋሽና የልጆቹን ጉድለቶች በመሙላት ደስ የሚሰኝ ነው። ከበሩ ላይ የቆመው ጐረቤት የፈለገውን ነገር ለማግኘት እያንኳኳ መቆየት ነበረበት፤ እግዚአብሔር ግን ለልጆቹ ጩኸት ፈጣን ምላሽ ይሰጣል (18፡1–8)።

መልእክቱ ግልጽ ነው፤ ይኸውም አንድ ሰው እሺ በማይለው ወዳጁ በር ላይ ቆሞ ለረዥም ጊዜ ሳያቋርጥ በማንኳኳት የሚፈልገውን

ካገኙ፥ ወደ አፍቃሪ ሰማያዊ አባታችን ሳናቋርጥ ስንጸልይ ምን ያህል በረከት እንደምናገኝ ነው። እኛ በቤት ውስጥ ከእርሱ ጋር የምንኖር ልጆቹ ነን።

በምሥራቁ ዓለም እንግዳ መቀበል መሠረታዊ ሕግ ነበር (ዘፍጥ. 18፡ ከ1 ጀምሮ)። አንድ ሰው እንግዳ ለመቀበል ባይፈልግ በመንደሩ ሁሉ ላይ አሳፋሪ ስም ስለሚያመጣ ጎረቤቶቹ ከእርሱ ጋር አይተባበሩም። በቤት ውስጥ የነበረው ሰውዬ ይህንን ስለሚያውቅ፥ ራሱን፥ ቤተሰቡን ወይም መንደሩን ለማሳፈር አልፈለገም፤ ስለሆነም ብድግ ብሎ ወዳጁ የሚፈልገውን ነገር አደረገለት።

የሰማዩ አባታችን ጸሎትን የሚመልሰው ለምንድን ነው? ለልጆቹ የጐደለውን ነገር ለማሟላት ብቻ ሳይሆን፥ የልጆቹን ፍላጐት በማሟላት ለስሙ ክብር ለማምጣት ጭምር ነው። «ስምህ ይቀደስ።» የእግዚአብሔር ሰዎች ሲጸልዩ የእግዚአብሔር ስም በአጠያያቂ ሁኔታ ላይ ይሆናል። ለልጆቹ እንክብካቤ የሚያደርግበት መንገድ ሊታመን እንደሚችል ለዓለም ይመሰክራል። ፊሊጽስ ብሩክስ እንደሚሉት፥ ጸሎት የእግዚአብሔርን እምቢታ ማሸነፍ ሳይሆን ለማድረግ ያለውን ፈቃደኛነት ይዞ መጠቀም ነው። ሳያቋርጡ መጸለይ የእግዚአብሔርን አሳብ ለማስለወጥ የሚደረግ ጥረት አይደለም። («ፈቃድህ በምድር ትሁን» ስለሚል)፥ መልስ ሊሰጠን ወደሚችልበት ስፍራ ራሳችንን ማድረስ ነው»

<u>ለጸሎት የተሰጡ የተስፋ ቃሎች</u> (ቁጥር 9–13)። የእነዚህ ግሦች የጊዜ አመልካች አስፈላጊ ነው፤ ይኸውም «ሳታቋርጡ ጠይቁ... ሳታቋርጡ ፈልጉ... ሳታቋርጡ አንኳኩ» የሚል ፍች ስለሚሰጡ ነው። በሌላ አባባል፥ ይህ ወደ እግዚአብሔር ዘንድ መምጣት ያለብን ድንገተኛ አደጋ ሲደርስብን ብቻ መሆን እንደሌለበት ያሳየናል፤ ይልቁንም ከአባታችን ጋር የማያቋርጥ ኅብረት ሊኖረን ያሻል። ኢየሱስ ይህንን «በእኔ ኑሩ» በማለት ሲገልጽ (ዮሐ. 15፡ከ1 ጀምሮ)፥ ጳውሎስም «ሳታቋርጡ ጸልዩ» ሲል መክሯል (1ኛ ተሰ. 5፡17)። በምንጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር አንድም መልሱን ይሰጠናል አልያም ለምን እንደማይመልስልን ያሳየናል። ከዚያ በኋላ አባታችን መልሱን እንዲሰጠን የሚያስፈልገውን ሁሉ ማድረግ የእኛ ድርሻ ይሆናል።

ትምህርቱ የእግዚአብሔርን አባትነት ገልጦ በማየት እንደ ተፈጸመ ልብ በል (ቁጥር 11–13)። እርሱ ስለሚያውቀንና ስለሚወደን፥ ለእኛ በሚሰጠን መልሶች ማፈርም ሆነ መፍራት የለብንም። አሁንም

ኢየሱስ ከአነስተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ያነጻጽራል፤ ምድራዊ አባት ለልጆቹ ከሁሉም የሚሻለውን ነገር የሚሰጥ ከሆነ፥ ሰማያዊው አባት ያለጥርጥር ከዚህ የሚበልጥ ያደርጋል። ይህም በብሉይ ኪዳን ለተወሰኑ ጥቂት ቡድኖች ተጠብቀው የነበሩትን በረከቶችና የመንፈስ ቅዱስን መልካም ስጦታዎች ይጨምራል (ቁጥር 13፡እና ማቴ. 7፡11)።

## 2. ሰይጣን (11፡14-28)።

ክስ (ቁጥር 14-16)። ይህ ጌታችን ሦስተኛው አጋንንትን የማስወጣት ተግባር የፈጸመውና ጠላቶቹ የሰይጣን ማኅበርተኛ ነው በማለት የከሰሱበት ነው (ማቴ.9፡32-34 እና 12፡22-37)። እግዚአብሔር አዳኝን በመላኩ እንደ መደሰት ፋንታ፥ የሃይማኖት መሪዎች በእግዚአብሔር ቃል እውነት ላይ ያምፁና የክርስቶስን ሥራና ባሕርይ እርባና-ቢስ ለማድረግ ይፍጨረጨሩ ነበር። ሰዎች የእግዚአብሔርን ሥራ ከሰይጣን ሥራ ለመለየት እስኪቸገሩ ድረስ መታወራቸውን በምናባዊ እይታ ተመልከት።

«ብዔል ዜቡብ» በኣል ከተባለው የፍልስጥኤም አምላክ ስሞች አንዱ ሲሆን (2ኛ ነገሥ. 1፡1-3)፥ «የዝንቦች ጌታ» የሚል ፍች አለው። ይህ ቃል በሌላ መልኩ «ብዔል ዜቡል» ተብሎ የሚጻፍ ሲሆን፥ ትርጉሙም «የማደሪያ ጌታ» የሚል ነው (የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሳችን ግን በሁለቱም ስፍራዎች «ብዔል ዜቡል» ስለሚል ልዩነቱን አያሳየንም)፤ ይኸው ሁለተኛው ፍች ከቁጥር 18-26 ከተጠቀሰው የክርስቶስ ማብራሪያ ጋር ይዛመዳል። አይሁዶች ብዙውን ጊዜ ስለ ሰይጣን ሲናገሩ በዚህ ስም ይጠቀማሉ።

በቁጥር 16 ላይ የሚገኘው ጥያቄ የክሱ ክፍል ነው። «እውነት ለእግዚአብሔር የምትሠራ ከሆነ፥ በምድር ላይ ተአምር መሥራት ብቻ ሳይሆን ከሰማይ ምልክት በማውረድ አረጋግጥልን» ሲሉ ጠይቀዋል። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን እየፈተኑ ሲሆን፥ ይህም አደገኛ ነገር ነበር።

ማፍረሻ (ቁጥር 17-22)። ኢየሱስ በሦስት ነጥቦች ለክሳቸው ምላሽ ሰጥቷል። በመጀመሪያ ደረጃ፥ ክሳቸው መሠረተ-ቢስ (ኢ-አመክኖአዊ) ነበር። ሰይጣን ከራሱ ጋር በመዋጋት መንግሥቱን የሚከፋፍለው ለምንድን ነው? (ኢየሱስ ሰይጣን ጠንካራና አንድነት ያለው ትክክለኛ መንግሥት እንዳለው እንደ ገለጸ ልብ በል። ኤፌ. 2፡1-3፤6፡ከ10 ጀምሮ ተመልከት)። ሁለተኛ፥ ክሶቻቸው ራሳቸውን የሚያመለክቱ ነበሩ፤ አይሁዶች አጋንንት የሚያስወጡት በምን ኃይል

ነበር? የእነርሱ *ሥራዎች* ከክርስቶስ *ሥራዎች* የሚለዩት እንዴት ነበር? በተቃራኒው በ*ሥራ* ላይ ያለው የእግዚአብሔር መንግሥት እንጂ የሰይጣን መንግሥት እንዳልሆነ የክርስቶስ ተአምራት ያሳያሉ!

በመጨረሻም፥ ክሳቸው በኃይሉ እንዳመኑ ያሳያል– ከሰይጣን የበለጠ ኃይል ባይኖረው ኖሮ፥ ሰይጣንን አያሸንፈውም ነበርና። ኢየሱስ ሰይጣንን የብረት ልብስ ለብሶ ቤተ መንግሥቱንና ዕቃዎቹን እንደሚጠብቅ ወታደር ገልጾታል። ይህም ሆኖ፥ ኢየሱስ የሰይጣንን ግዛት በመውረር የብረት ልብሱንና መሣሪያዎቹን አውድሞአል፤ ምርኮንም በዝብዞአል! (ቈላ. 2፡15፤ ዮሐ. 12፡31–33፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡8 ተመልከት)። ጌታችን ምርኮን በመማረክ (ኤፌ. 4፡8) እስረኞችን ነፃ አውጥቷል (ሉቃ. 4፡18)። ምንም እንኳ የተወሰነ ሥልጣን እንዲኖረው የተፈቀደለት ቢሆንም፥ ሰይጣን የተሸነፈ ጠላት ነው።

<u>የሕይወት ተዛምዶ</u> (ቁጥር 23–28)። በዚህ መንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ ገለልተኛ መሆን አይቻልም (ቁጥር 23፤ በተጨማሪ 9፡50ን ተመልከት)፤ ገለልተኛ መሆን ማለት ከክርስቶስ ጋር የሚቃረን አቋም መያዝ ነውና። በዚህ ዓለም ሁለት መንፈሳዊ ኃይላት ሥራቸውን ያከናውናሉ፤ እኛም ከሁለቱ አንዱን መምረጥ አለብን። ሰይጣን በመበታተንና በማጥፋት ላይ ሲገኝ፥ ኢየሱስ ግን በመሰብሰብና በማነጽ ላይ ነው። ስለሆነም፥ አንዱን መምረጥ ይኖርብናል፤ አንዱን ካልመረጥን ግን ያለ ጥርጥር ከክርስቶስ ጋር የሚቃረን አቅጣጫ ይዘናል ማለት ነው።

ኢየሱስ የሰውዬውንና የርኩስ መንፈስን ታሪክ በመናገር የገለልተኛነትን አደገኛነት አብራርቷል። የሰውዬው አካል የርኩስ መንፈሱ «ቤት» ነበር (ቁጥር 24ን ተመልከት፤ ቁጥር 17 እና 21)። ባልታወቀ ምክንያት ነዋሪው ጋኔን «ቤቱ»ን ጥሎ ወደ ሌላ ስፍራ ይሄዳል። የሰውዬው ሁኔታ ወዲያውኑ መልካም ለውጥ ማሳየት ይጀምራል፤ ዳሩ ግን ሰውዬው እግዚአብሔር ወደ ውስጡ ገብቶ እንዲኖር አልጋበዘም። በሌላ አባባል ሰውዬው ገለልተኛ ሆኖ ቆየ። ምን ተከሰተ? ጋኔኑ ከእርሱ የከፉትን ሰባት ሌሎች ጋኔኖች ይዞ ተመለሰ፤ የሰውዬውም ሁኔታ ጭራሽ ተበላሸ።

ኦስዋልድ ቻምበርስ ሲጽፉ፥ «በሃይማኖት ላይ ገለልተኛ አቋም መያዝ ሁልጊዜም ፈሪነት ነው። እግዚአብሔር ደግሞ በምርጫ የተወጠነውን የገለልተኝነት ፍርሃት ወደ ሽብር ይለውጠዋል» ብለዋል።

ከኢየሱስ ጐን መቆም ማለት፥ «የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው» ስትል በጩኸት እንዳስተጋባችው ሴት (ቁጥር 27) ትክክለኛ ነገሮችን ከመናገር የዘለቀ ነው። ሴትዮዋ ያለ ጥርጥር ከልቧ የተናገረች ቢሆንም፥ ያ ብቻ በቂ አልነበረም። ከኢየሱስ ክርስቶስ ጐን የምንቆመው ቃሉን ሰምተን ስንታዘዘው ነው (6፡46-49 እና 8፡19-21 ተመልከት)።

## 3. የተከፈተ በር (11፡29-36)

በልባቸው የነበረውን ስለሚያውቅ ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን ያህል በበርካታው ሕዝብ አይደሰትም ነበር። አሥራ ሁለቱ በ«ስኬት» እንዳይወሰዱ ለመከላከል፥ ኢየሱስ ቃሉን በሚያገለግሉበት ጊዜ ሊከሰቱ የሚችሉትን አንዳንድ ሁኔታዎች አስገነዘባቸው። መንፈሳዊ የአገልግሎት በሮች ያላቸውን አስቸጋሪነት ለማሳየት ሦስት ማብራሪያዎችን ተጠቀመ።

ዮናስ (ቁጥር 29-30፥32)። መሪዎች መሚሕነቱን ለማረጋገጥ ምልክት ያሳያቸው ዘንድ ያለማቋረጥ ይጠይቁት ነበር። የነገራቸው አንድ ብቸኛ ምልክት የነቢዩ ዮናስ ምልክት ሲሆን፥ ይህም ሞት፥ ቀብርና ትንሣኤ ነው። ጌታችን መሚሕና የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የተረጋገጠው ከሞት በመነሣቱ ሲሆን (ሮሜ 1፡4)፥ ጴጥሮስ በበዓለ ኀምሳ ዕለት ለእስራኤላውያን የሰበከውም ይህንኑ ነበር (የሐዋ. 2፡ከ22 ጀምሮ)። የቀድሞ ቤተ ክርስቲያን ምስክርነት ትንሣኤውን ያማከለ ነበር (የሐዋ. 1፡22፤3፡15፤5፡30-32፤13፡32-33)። ዮናስ የሚታይ ተአምር ሲሆን፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እንዲሁ ነበር።

ሰሎሞን (ቁጥር 31)። በዚህ ስፍራ አጽንኦት የተሰጠው በንጉሡ ጥበብ ላይ እንጂ በነቢዩ ተግባር ላይ አይደለም። ንግሥት ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ብዙ ኪሎ ሜትሮች አቋርጣ ተጉዛለች (1ኛ ነገሥ. 10)፤ በዚህ ስፍራ ግን ራሱ የእግዚአብሔር ልጅ በመካከላቸው ሳለ አይሁዶች ቃሉን ለማመን አልፈለጉም ነበር! ኢየሱስ ምልክት ቢያሳያቸው እንኳ ልባቸውን አይለውጠውም ነበር። የእግዚአብሔር ሕያው ጥበብ በሚያስፈልግበት ጊዜ ባረጀና ባፈጀ ሃይማኖታዊ ወጋቸው ረክተው ተቀመጡ።

የእነዚህ ማብራሪያዎች ጠቀሜታ አሕዛብንም መጨመራቸው ነው። ዮናስ በነነዌ ለነበሩት አሕዛብ ሲሰብክ ንስሐ ገብተው ድነዋል። ከአሕዛብ ወገን የሆነች ንግሥት ስለ ሰሎሞን ጥበብ ስትሰማ ከማድነቅ አልፋ አምናለች። ይህ ሁሉ ዕድል እያላቸው አይሁዶች ባያምኑ፥

የነነዌ ሕዝቦችና የሳባ ንግሥት በመጨረሻው ፍርድ ቀን በእነርሱ ላይ ምስክሮች ሆነው ይቆማሉ። ጌታ ለእስራኤላውያን አያሌ ዕድሎችን ቢሰጣቸውም አምነው ሊጠቀሙባቸው አልፈለጉም (13፡34-35፤ ዮሐ. 12፡35-41)።

ሦስተኛው ማብራሪያ ከታሪክ ሳይሆን ከዕለታዊ ሕይወት የተወሰደና ከዚህ በፊትም ኢየሱስ የተጠቀመበት ነው (ማቴ. 6፡22-23)። የእግዚአብሔር ቃል በዚህ ጨለማ ዓለም ላይ የሚያበራ ብርሃን ነው [መዝ. (119)፡105፤ ምሳ. 6፡23]። ይህም ሆኖ፥ የብርሃን በውጭ መብራት ብቻ በቂ አይደለም፤ ምንም መልካም ተግባር ከመከናወኑ በፊት ወደ ሕይወታችን ውስጥ መግባት አለበት «የቃልህ ፍቺ ያበራል፥ ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል» [መዝ. (119)፡130]። እጅግ የደመቀች ፀሐይ አንድን ዓይነ ስውር እንዲያይ ልትረዳው አትችልም።

በኢየሱስ ክርስቶስ በምናምንበት ጊዜ ዓይኖቻችን ተከፍተው ብርሃን ወደ ሕይወታችን ይዘልቅና የብርሃን ልጆች እንሆናለን (ዮሐ. 8፡12፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡3-6፤ ኤፌ. 5፡8-14)። ዋናው ብርሃኑን በመጠቀም በእምነት ብቻ መመላለሳችን ነው። አንድ ዓይናችንን በእግዚአብሔር ነገሮች ላይ ሌላውን ደግሞ በዓለም ላይ ብናደርግ (1ኛ ዮሐ. 2፡16)፥ ብርሃኑ ወደ ጽለመት ይለወጣል! እግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ እንድንገዛለትና እንድንታዘዝለት ስለሚፈልግ (ቁጥር 23) ክርስቲያን «በድንግዝግዝ ብርሃን» ሊመላለስ አይችልም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ሦስት ሰዎች ይህንን እውነት ያብራራሉ። ልባቸው በመከፈሉም ምክንያት በብርሃን የጀመሩትን ጉዞ በጽልመት ደምድመዋልና። ሳምሶን የሚለው ስም «ፀሐያማ» የሚል ፍቺ ሳይኖረው አይቀርም፤ ይህም ሆኖ «ለሥጋ ምኞት» በመገዛቱ በጨለማ ክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውር ባሪያ ሆኖ አለፈ (መሳ. 16)። ሎጥ ከአጎቱ አብርሃም ጋር የእምነት ጉዞ (ምናኔ) ጀመረ። ይሁንና፥ «ለዓይን አምሮት» (ዘፍ. 13፡10-11) በመገዛቱ ሰክሮ ከልጆቹ ጋር ዝሙት ፈጽሞአል (ዘፍ. 19፡30-38)። ሎጥ ለሁለት ጌቶች ሊገዛና በሁለት አቅጣጫዎች ሊመለከት ፈለገ።

ንጉሥ ሳኦል ንግሥናውን የጀመረው እንደ ትሑት መሪ ቢሆንም፥ ትዕቢቱ ወደ ጠንቋይ ሴት ዋሻ መራው (1ኛ ሳሙ. 28)፤ በመሆኑም በጦር ሜዳ ላይ ራሱን ገደለ (1ኛ ሳሙ. 31)። ኃጢአቱ በሕይወቱ የሞላው ትዕቢት ሲሆን፤ ራሱን አዋርዶ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሊታዘዝ አልቻለም።

እያንዳንዳችንን የሚቆጣጠረን አንድም ብርሃን አልያም ጨለማ ነው። እጅግ የሚያስፈራ ነገር ቢኖር አንዳንድ ሰዎች በጌታ ላይ ልባቸውን በማደንደናቸው ብርሃንን ከጨለማ ለመለየት አለመቻላቸው ነው። የጨለማን ፈለግ ተከትለው ሲኑ ሳለ በብርሃን የሚመላለሱ ይመስላቸዋል። ጻፎችና ፈሪሳውያን ሕጉን ሲያጠኑ ብርሃንን እንደሚያዩ ቢናገሩም፥ በጨለማ ውስጥ ይኖሩ ነበር (ዮሐ. 12፡35-50 ተመልከት)።

## 3. ግብዝነት (11፡37-54)።

የሃይማኖት መሪዎች ያጠፉት ዘንድ ጥረት በሚያደርጉበት በዚህ የክርስቶስ አገልግሎት ወቅት፥ ፈሪሳዊው ምግብ የጋበዘው ለምን ይሆን? በእውነተኛ ልብ እውነትን የሚፈልግ ሰው ቢሆን ኖሮ ከጌታችን ጋር በግል ይነጋገር ነበር። ስለሆነም ኢየሱስን ለመክሰስ አጋጣሚ የሚፈልግና ኢየሱስ ከምግብ በፊት የሚደረገውን የመታጠብ ሥርዓት በጣሰ ጊዜ ምክንያት እንዲያገኝበት ያሰበ ይመስላል (ማር. 7፡2-3)። በጋባዥነት የሚያስተናግደውን ሰውዩ አሳብ በመረዳቱ፥ ኢየሱስ በፈሪሳውያን ላይ «መንፈሳዊ ግምገማ» በማቅረብ ምላሽ ሰጠ።

<u>ሞኝነታቸውን አጋለጠ</u> (ቁጥር 37-41)። የፈሪሳውያን መሠረታዊ ስሕተት ጽድቅ የውጫዊ ተግባራት ጉዳይ ብቻ እንደሆነ በማሰብ ውስጣዊ ዝንባሌዎችን ማንኳሰሳቸው ነበር። የውጭውን ለማጽዳት በጣም ሲጠነቀቁ በውስጣቸው ግን ኃጢአት ያስተናግዱ ነበር። የውጭውንም የፈጠረው ያው አንዱ አምላክ መንጻት የሚያሻውን «ውስጣዊ ሰውነትም» እንደፈጠረ የዘነጉ ይመስላል [መዝ. (51)፡6፥10]።

ፈሪሳውያን ስለ ልግስናቸው በመናገር የሚመጻደቁ ሲሆን (ማቴ. 6፡1-4፤ ሉቃ. 18፡11-12)፥ ዳሩ ግን ከውስጥ ያለውን ለጌታ አልሰጡም ነበር። የውጭውን ንጹሕ ማድረግ የሚቻለው የውስጡን በማንጻት ነው (ቁጥር 41)። ኬኒት ዌስት ይህንን ቁጥር፥ «ይልቁንም ከውስጥ ያሉትን ነገሮች እንደ ምጽዋት ስጡ፤ ከዚያ በኋላ ሁሉም ነገር ንጹሕ ይሆንላችኋል» ሲሉ ይፈቱታል። የቆሸሸ እንደበት የሚገራው ጥርስን በሳሙና በማጠብ ሳይሆን ልብን በማንጻት ነው።

<u>ኃጢአታቸውን አወገዘ</u> (ቁጥር 42-52)። እነዚህ ስድስት «ወዮዎች» በማቴዎስ 23 ውስጥ ከሚገኙ «ወዮዎች» ጋር ይመሳሰላሉ። ኢየሱስ ከፈሪሳውያን ኃጢአቶች ጀመረና ወደ ጻፎች ኃጢአቶች ተዛወረ፤

ይህንንም ያደረገው የፈሪሳውያንን አሠራር ያስከተለው የጻፎች የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም በመሆኑ ነው (ቁጥር 45–52)።

የመጀመሪያዎቹ ሦስት «ወዮዎች» ፈሪሳውያንን ለተሳሳተ የቅድሚያ አሰጣጣቸው ያወግዛሉ። ከአነስተኛ ቅጠላቅጠሎችና የቅመም ዘር ሳይቀር አሥራት ለማውጣት ሲጠነቀቁ እንደ ፍትሕና ፍቅር ያሉትን አስፈላጊ ነገሮች ይዘነጉአቸዋል (ሚክ. 6፥7–8)። በአናሳ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ያደርጉ ነበር። ኢየሱስ የተናገረው አሥራት ማውጣት እንዲያቆሙ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ሃይማኖታዊ ተግባሮቻቸውን በተገቢው መንገድ እንዲያከናወኑ ነው።

እንዲሁም፥ ደግሞ ዝናን ከባሕርይ አልቀው ይመለከቱ ነበር። በተገቢ ወንበሮች ላይ መቀመጡና በታዋቂ ሰዎች መሞገሱ መንፈሳውያን እንደሚያደርጋቸው ያስቡ ነበር። ዝና ሰዎች ማንነታችንን የሚገምቱበት ሲሆን፥ ባሕርይ ግን እግዚአብሔር ማንነታችንን የሚያውቅበት አሳብ ነው።

በቁጥር 44 ላይ የቀረበው ማወዳደር በእንግድነት የተቀበለውንና በዚያ የነበሩትን ሌሎች ፈሪሳውያን ሳያስቆጣ አይቀርም። አይሁዶች የሞተ ሰው በመንካት ላለመርከስ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጉ ስለነበር (ዘኁል. 19፥11–22፤ በተለይም ቁጥር 16ን ተመልከት)፥ መቃብሮች በትክክል መለሰናቸውን ለማረጋገጥ ይተጉ ነበር። ፈሪሳውያን ግን መቃብር እንደማይመስሉ ያልተለሰኑ መቃብሮች ነበሩ። ይህም ማለት ሌሎች ሰዎች ይበልጥ ቅዱሳን እንደሆኑ እንረዳለን እያሉ ሳያውቁ እያረከሱአቸው ነበር። ፈሪሳውያን ሰዎችን በመርዳት ፈንታ ይጐዱአቸው ነበር።

ጻፎች የጌታችን የቃላት ውጋት ስለተሰማቸው ራሳቸውን ለመከላከል ሞከሩ። ኢየሱስ ለእነርሱ ምላሽ ለመስጠት ሦስት ማብራሪያዎችን ተጠቅሟል– ሸክሞች፥ መቃብሮችና ቁልፎች።

ጻፎች በሰዎች ሸክም ላይ ለመጨመር ቢተጉም፥ ሸክሙን እንዲያነሡ የሚረዳ ልብ አልነበራቸውም። የእግዚአብሔር የቃሉ «አገልጋዮች» በችግር ውስጥ ላሉት ሰዎች ተጨማሪ ችግር መፍጠራቸው ምንኛ የሚያሳዝን ነገር ነው! አንድ መጋቢ ወዳጄ በየዕለቱ፥ «ጌታ ሆይ፥ በማንም ችግር ላይ ሌላ እንዳልጨምር እርዳኝ» እያለ ይጸልያል። ኢየሱስ በማቴዎስ 11፥28–30 የተጠቀሰውን የቸርነት ግብዣ ሲያደርግ እነዚህን «ሃይማኖታዊ ሸክሞች» እያሰበ ነበር።

በተጨማሪም፥ ጻፎች የቀደመውን ወግ አምረው የታዩ በማድረግ እና እነርሱ በነበሩበት የሃይማኖት ተቋም የተሠዉትን ነቢያት በማክበር በኩል ጉበዞች ነበሩ። ከመጽሐፍ ቅዱስ እና ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንመለከተው፥ ብዙውን ጊዜ እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮች አገልግሎታቸው በይበልጥ በሚያስፈልጉአቸው ሰዎች አይወደዱም፤ ይሁንና ቀጣዩ ትውልድ እነዚህን አገልጋዮች ያከብራቸዋል። ፈሪሳውያን ልክ እንደ «ተሰወሩ መቃብሮች» ሲሆኑ፥ ጻፎች ደግሞ ማለፊያ መቃብሮች ሠርተዋል።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የመጀመሪያው ሰማዕት አቤል ሲሆን፥ የመጨረሻው ዘካርያስ ነው (ዘፍ. 4፡1–15 እና 2ኛ ዜና 24፡20–27 ተመልከት፤ በዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ 2ኛ ዜና የመጨረሻው መጽሐፍ ነው)። ኢየሱስ ጻፎችና ፈሪሳውያን ለብሉይ ኪዳን ነቢያት መገደል የግል ኃላፊነት እንዳለባቸው አልተናገረም። እርሱ የሚለው ልክ እንደ ጻፎችና ፈሪሳውያን ዓይነት ሰዎች በእግዚአብሔር አገልጋዮች ላይ እነዚህን አስከፊ ነገሮች እንደፈጸሙ ነው። የእነዚህ ሰዎች የመጨረሻ ጥፋት የእግዚአብሔርን ልጅ መስቀል ይሆን ነበር።

በመጨረሻም፥ ጻፎች ለተራው ሕዝብ የእግዚአብሔርን እውቀት ያለመስጠት ጥፋት ነበረባቸው። የራሳቸው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አለመግባት የከፋ ሆኖ ሳለ፥ ሌሎችም እንዳይገቡ ያግዱ ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ከበድ ያለ ኃላፊነት ነውና ማንኛውም ተራ ሰው እንዲሁ ማስተማር አይገባውም (ያዕ.3፡1)። የሚያሳዝነው «የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት» የሚሉት ነገር አንዳንድ ያልተዘጋጁ ሰዎች አለማወቃቸውን የሚያንጸባርቁበት መድረክ ነው።

ለዚህ ነገር ሌላም ገጽታ አለው፡– ጻፎች ከተማሩና ሥልጣን ካላቸው መምህራን በቀር ማንም ሰው ሕጉን ሊረዳና ሊያብራራ እንደማይችል በመግለጽ ሕዝቡን አሳምነው ነበር። ዛሬም ያ የትዕቢት አመለካከት አንዳንድ ጊዜ ራሱን ሲያንጸባርቅ እናያለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋዎች ላይ ከሚገባው በላይ ትኩረት የሚያደርጉ ሰዎች፥ መንፈስ ቅዱስ ግሪክና ዕብራይስጥ ለማያውቅ ሰው ሊያስተምር እንደማይችል ለሕዝቡ ለማሳየት ይሞክራሉ። «ዛሬ አንድ ተማሪ ከተራ መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ነገር ይማር ይሆን?» ብለህ እንድትደነቅ የሚያደርጉ አያሌ «የማጥኛ መጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎች» አሉ። (ከእነዚህም ብዙዎቹ ጠቃሚዎች ናቸው)። እውነተኛ ክርስቲያናዊ ምሁርነትን ልንንቅ አይገባም፤ ያም ቢሆን ደግሞ ነገሮችን ሚዛናዊ ማድረግ አለብን።

ኢየሱስ ክርስቶስ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ነው (24፡44-48)። ቁልፉን ስታስወግድ እግዚአብሔር የጻፈውን ነገር ልትረዳ አትችልም። የሥነ-መለኮት ጥናቶች አስፈላጊዎች እንደሆኑ ሁሉ፥ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እጅግ የላቁ መመዘኛዎች የተሰጠ ልብና የሚታዘዝ ፈቃድ ናቸው። በራሴ የአገልግሎት ዘመን የማውቃቸው አንዳንድ የላቁ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች በጉልበታቸው ተንበርክከውና በሕይወት ጦር ሜዳ ውስጥ አልፈው የእግዚአብሔርን ቃል እውነት የተማሩ ናቸው። ያስተማራቸው መንፈስ ቅዱስ እንጂ ሰው አይደለም።

<u>ቁጣቸውን ቀሰቀሰ</u> (ቁጥር 53-54)። ግብዞች ለዝናቸው መጓደል አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ ኃጢአታቸው እንዲገለጽ አይፈልጉም። ጌታን ከመቃወም ይልቅ፥ እነዚህ ሰዎች ከፊቱ በመውደቅ ምሕረት ሊጠይቁት ይገባ ነበር። አንድ የተሳሳተ አሳብ አግኝተው ሊያስሩት ተስፋ በማድረግ ሆን ብለው «በማጥመጃ ጥያቄዎች» ያውኩት ነበር። ይህ የእግዚአብሔርን ልጅ ለማስተናገድ ምንኛ አሳፋሪ መንገድ ነው።

የሆነ ሆኖ፥ ዛሬም ጥንት ጻፎችና ፈሪሳውያን የተሟገቱላቸው ዓይነት ሃይማኖታዊ መዋቅሮች አሉ። መሪዎች ቃሉን ተርጉመው ለተከታዮቻቸው ያቀርባሉ፤ በዚህ ላይ ማንም ሰው መሪዎቹን የሚያሳፍሩ ጥያቄዎችን ለማንሣት ወይም የተቃውሞ አሳብ ለመሰንዘር አይችልም። በዚህ ዓይነት መሪዎቹ ሕዝቡን የሚበዘብዙ ሲሆን፥ ሸክማቸውን ለማቃለል የሚወስዱት እርምጃ እጅግ አናሳ ወይም ምንም ነው። ከሁሉም የሚከፋው ደግሞ መሪዎቹ የራሳቸውን ኃጢአት ለመሸፈን በመዋቅሩ መጠቀማቸው ነው። የእግዚአብሔር እውነት ነፃ ሊያወጣን ቢገባም፥ እነዚህ ቡድኖች ግን ሰዎችን ወደ ላቀ እስራት ይመራሉ።

እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ መምህራንን ስለ ሰጠ ልንሰማቸው ይገባል (ኤፌ. 4፡11)። ይህም ሆኖ፥ እውነትን እንደሚያስተምሩ ለማረጋገጥ የምንሰማውን በቅዱሳት መጻሕፍት ማመሳከር አለብን (1ኛ ተሰ. 5፡19-21)፤ እንዲሁም፥ ማንም ሰው ወደ ባርነት እንዲመራንና እንዲበዘብዘን መፍቀድ የለብንም (2ኛ ቆሮ. 11፡20)።

የእግዚአብሔርን ቃል ብርሃንና የጸሎትን ዕድል ማግኘት መታደል ነው። ጠላት ግን የመንፈሳዊ ዕድገትንና ነፃነትን በረከቶች ሊነጥቀን ይፈልጋል። ዕቅዱም በእውነት ፋንታ ግብዝነትን እንድንይዝ ከውስጡ ይልቅ በውጪው ላይ ይበልጥ እንድናተኩር ማበረታታት ነው፤ ይህም ባሕርይን በማንኳሰስ ዝናን እንድንሻ ነው።

ይህ እጅግ የከበደ ነገር በመሆኑ፥ ኢየሱስ በምዕራፍ 12 በዚህ ጉዳይ ላይ የሚጨምረው አለው። እኛም በመካከሉ ልንጠነቀቅ ይገባል!

## - 11 -

# አማኝ ሆይ፥ ተጠንቀቅ!

### ሉቃስ 12

ላይገነዘቡት ቢችሉም የጌታችን ደቀ መዛሙርት በከፍተኛ አደጋ ውስጥ ነበሩ። በአንድ በኩል፥ መንፈሳዊ እውነትን ለመስማት ሳይሆን ዳሩ ግን ኢየሱስ አንድ ተአምር ሲሠራ ወይም አንዳንድ የግል ችግሮችን ሲፈታ ለማየት በሚፈልጉ በርካታ ሕዝብ ተከብበው ነበር። በሌላ በኩል፥ ጸፎችና ፈሪሳውያን ኢየሱስን ለማስወገድ ታላቅ ሤራ እያውጠነጠኑ ነው። ታዋቂነትን መፈለግና ሰውን መፍራት ለአያሌ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሕይወት መበላሸት ምክንያት ሆኗል።

በምዕራፍ 12፥ ሉቃስ የጌታችንን አምስት ማስጠንቀቂያዎች መዝግቦአል። ታማኝ ደቀ መዛሙርት ለመሆን ከፈለግን ዛሬ ከእነዚህ ማስጠንቀቂያዎች አራቱን ልብ ብለን መመልከት አለብን። ከደኅንነት ርቆ የጠፋው ዓለም ደግሞ አምስተኛውን ማስጠንቀቂያ ልብ ይለው ዘንድ የግድ ነው።

### 1. ከግብዝነት ተጠንቀቁ (12፡1-12)

ግብዝ የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ በተውኔት ውስጥ ያለውን «ተዋናይ» ከሚያመለክት ቃል የተወሰደ ነው። በሁሉም የሕይወት እርምጃ ውስጥ፥ የራሳቸውን እውነተኛ ማንነት ለመደበቅ ሲሉ ሌሎችን ለማስደሰት የሚፈልጉ ግብዞች አሉ። በክርስትና ሕይወት፥ ግብዝ ማለት ካለው የበለጠ መንፈሳዊ መስሎ ለመታየት የሚፈልግ ሰው ነው። እነዚህ ሰዎች አስመሳዮች መሆናቸውን ቢያውቁም፥ ማንም ሰው የማይደርስባቸው መስሎ ይታያቸዋል። የክርስትና ሕይወታቸው ግን ከንቱ ማስመሰያ ብቻ ነው።

ኢየሱስ በዚሁ ወቅት ለምን ይህንን ማስጠንቀቂያ እንደሰጠ መመልከቱ ቀላል ነገር ነው። ደቀ መዛሙርቱ አንድም ሕዝቡን በማስደሰት ተወዳጅነትን ሊያተርፉ አልያም ጸፎችና ፈሪሳውያንን በማስደሰት ከመከራ ሊድኑ ሳይፈተኑ አልቀሩም። ሁላችንም ሰዎች እንዲወድዱን እንፈልጋለን፤ ስለሆነም፥ ሌሎች ለማየት የሚፈልጉትን «የትእይንት ክፍል መተመን» ቀላል ነገር ይመስለናል።

ግብዝነትን ከሕይወታችን ወዲያ ልናርቅ እንዴት እንችላለን?

በመጀመሪያ ደረጃ፥ ግብዝነት ምን እንደሆነ ማወቅ አለብን (ቁጥር 1)። ኢየሱስ ከእርሾ ጋር አወዳድሮታል፤ ይህም እያንዳንዱ አይሁዳዊ ከክፉ ነገር ጋር የሚያዛምደው ስያሜ ነው። (ዘፀአ. 12፡15–20 ተመልከት። ጳውሎስም እርሾን ኃጢአትን ለማመልከት ተጠቅሟል– 1ኛ ቆሮ. 5፡6–8፤ እና ገላ. 5፡9 ተመልከት።) እንደ እርሾ ሁሉ ግብዝነት በትንሹ ይጀምርና ሳይታወቅ በፍጥነት ያድጋል። ሲያድግም ጠቅላላውን አካል ይበክላል። እርሾ እንጀራ ይጋገር ዘንድ ለሊጡ የሚያደርገውን ድጋፍ ግብዝነትም ለሰው ስግብግብነት ይጠቅማል፤ ይኸውም (በትዕቢት) መነፋት ነው (1ኛ ቆሮ. 4፡6፥18–19፤5፡2 ተመልከት)። ወዲያው ትዕቢት ድል ይነሣና የሰውዬው ባሕርይ በፍጥነት ይበላሻል።

ግብዝነትን ከሕይወታችን ለማራቅ ከፈለግን የመጀመሪያዋን እናሳ «እርሾ» እንኳ እንዳትገባ መከልከል አለብን። አንድ ጊዜ ማስመሰል ከጀመርን ሂደቱ በቶሎ ይፋጠናል፤ እየቆየን ስንሄድ ይብስ መከፋቱን ይቀጥላል። ሰር ዋልተር እስኮት እንደ ጻፉት ፥–

«መቼ ዛሬ ሆነ
ድሩን ያደራነው፥
ገና መጀመሪያ
ያታለልን 'ለት ነው!»

ኢየሱስ ሁለተኛውንም ትምህርት ሰጥቷል፤ ይኸውም ግብዝነት ምኝነትና ከንቱ እንደሆነ ነው (ቁጥር 2–3)። ለምን? ምክንያቱም ሊደበቅ የሚችል ነገር የለምና። ኢየሱስ በዚህ ስፍራ በቀዳሚነት ያመለከተው ወደ ራሱ ትምህርቶች ቢሆንም፥ መመሪያው ለሌሎችም የሕይወት ክፍሎች ይሠራል። ምናልባትም ሕዝቡም ሆነ ፈሪሳውያኑ እንዳይቀየሙ አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት እውነቱን ለመሸፈን ወይም ከውሸት ጋር ለመስማማት ተፈትነው ይሆናል (8፡16–18 እና 11፡33 ተመልከት)። የእግዚአብሔር እውነት እንደ ብርሃን እንጂ እንደ እርሾ ስላልሆነ ሊደበቅ አይገባም። የግብዞች ውሸቶች አንድ ቀን ይጋለጣሉ፤ ስለዚህ ለምን በግብዝነታችን እንቀጥላለን? እስኪ ብርሃኑ ደምቆ ያብራ።

ሦስተኛ፥ የግብዝነትን መነሾዎች ማወቅ አለብን (ቁጥር 4–7)። ኢየሱስ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ «ፍርሃት» የሚለውን ቃል አምስት ጊዜ ጠቅሶታል፤ ይህም መሠረታዊ የግብዝነት መነሾ ሰውን መፍራት እንደሆነ ያስተምረናል። ሌሎች ስለ እኛ ምን እንደሚሉ ወይም ምን እንደሚያደርጉ በማሰብ ስንፈራ፥ ድጋፋቸውን እንዳይነፍጉን

ልናስደስታቸው እንፈልጋለን። ካስፈለገም ዓላማዎቻችንን ከዳር ለማድረስ እንዋሻለን፤ ይህም ግብዝነት ነው። የሚያሳዝነው ብዙዎቹ ጸፎችና ፈሪሳውያን እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ከሚያውቀው ባሕርይ ይልቅ ሰዎች ስለ እነርሱ በሚያስቡት ዝና ላይ ያተኩሩ ነበር። ሰውን መፍራት ሁልጊዜም ወጥመድ ያመጣል (ምሳ. 29፡25)። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ያንን ወጥመድ እንዲያስወግዱ ፈለገ።

የግብዝነት መፍትሔው ሰዎች የሚሉትንና የሚያደርጉብንን ነገር ዘንግቶ እግዚአብሔርን ብቻ በመፍራት መኖር ነው። እግዚአብሔርን በትክክል የሚፈራ ሰው ሌላ ማንኛውንም ዓይነት ነገር መፍራት ስለማይኖርበት፥ ፈሪሃ–እግዚአብሔር ሌሎችን ፍርሃቶች ሁሉ የሚያሸንፍ ነው። ሰው ሊያደርግ የሚችለው ነገር ቢኖር ሥጋን መግደል ነው፤ እግዚአብሔር ግን ነፍስን ይኮንናል! እርሱ የመጨረሻው ፈራጅ ስለሆነና ለዘላለምም ስለሚፈርድ፥ ፈሪሃ–እግዚአብሔርን ከሁሉም ነገር ማስቀደም አስተውሎታዊ ድርጊት ነው። አምላካችን ያውቀናል፤ ይጠነቀቅልናልም። እርሱ ለድንቢጦችም ይጠነቀቃል። እኛ ግን ከእነርሱ እንበልጣለን፤ እንግዲህ፥ ሰውን የምንፈራው ለምን ይሆን?

እዚህ ውስጥ ሌላ ነገርም ተከቷል፤ ይኸውም ለክርስቶስ በግልጽ መመስከር እንዳለብን ነው (ቁጥር 8–9)። ይህንን ካደረግን ግብዝነትን በቀላሉ እያስወገድን በእውነት ልንኖር እንችላለን። ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ በአብ ፊት እየመሰከረልን እንዳለ እያወቅን እንዴት ሰዎችን ልንፈራ እንችላለን? የሚያስፈልገው በምድር ላይ ሰዎች ስማችንን ማመስገናቸው ሳይሆን፥ እግዚአብሔር በሰማይ ስለ እኛ መመስከሩ ነው (2ኛ ጢሞ. 2፡8–14 ተመልከት)።

በመጨረሻም፥ <u>በመንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍ አለብን</u> (ቁጥር 10–12)። ኢየሱስ ከራሱ ጋር የሚቃረን ይመስላል። ከቁጥር 8–9 በግልጽ እንድንመሰክርለት ይፈልጋል፤ በቁጥር 10 ግን በእርሱ ላይ ቃል ልንናገርና ይቅርታ ልናገኝ እንደምንችል ይገልጻል። በመንፈስ ቅዱስ ላይ ቃል ብንናገር ግን ይቅርታ አናገኝም። ይህ ማለት መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ልጅ የበለጠ ክብር አለው ማለት ነው?

ይህ አባባል መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ውስጥና በሐዋርያት አማካኝነት ከሚፈጸመው አገልግሎት ጋር የተያያዘ መሆኑን ልብ በል (ቁጥር 11–12)። የአይሁድ ሕዝብ የመጥምቁ ዮሐንስን ቃል ሰምቶ ንስሐ ለመግባት ባለመፈለጉ እግዚአብሔር አብን አልተቀበለም ነበር፤ ዮሐንስ የተላከው በአብ ነውና ። ጲላጦስ እንዲሰቅለው በጠየቁት ጊዜ

እግዚአብሔር ወልድን አንቀበልም ብለዋል። ይህም ሆኖ፥ ገና የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ስለነበር ያ ኃጢአት ይቅር ሊባል ይችል ነበር።

እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ፈጥኖ አልፈረደም። ይልቁንም፥ ኢየሱስ በመስቀል በተሰቀለ ጊዜ ጸለየላቸው (23:34፤ በተጨማሪም የሐዋርያት ሥራ 3:17 ተመልከት)። ከዚያም እግዚአብሔር በሐዋርያትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚገኙ ሌሎች አማኞች አማካኝነት ያገለገለውን መንፈስ ቅዱስ ላከላቸው። ይህ ለሕዝቡ የተሰጠው የመጨረሻ ዕድል ሲሆን፥ መንፈስ ቅዱስን ባለመቀበል ተሳሳቱ (የሐዋ. 7:51)። መልእክቱ በመጀመሪያ ወደ አይሁዶች ሲሄድ፥ ሉቃስ 12:11-12 በመጀመሪያዎቹ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፎች ውስጥ ተፈጸመ (ሮሜ. 1:16፤ የሐዋ. 3:26፤13:46)። የእስራኤላውያን ሦስተኛው «ብሔራዊ ኃጢአት» እስጢፋኖስን መውገራቸው ነበር (የሐዋ. 7)፤ ከዚያም በኋላ መልእክቱ ወደ ሰማርያውያን (የሐዋ. 8) እና ወደ አሕዛብ (የሐዋ. 10) ተዛመተ። እስጢፋኖስ፥ «ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ» እንዳለ ልብ በል (የሐዋ. 7:51)።

ከምእተ ዓመታት በፊት በእስራኤላውያን እንደተፈጸመው ዓይነት በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚፈጸም ኃጢአት ዛሬም በሰዎች ይፈጸማል ብዬ አላምንም። ዛሬ ብቸኛው «ስርየት የሌለው ኃጢአት» ኢየሱስ ክርስቶስን እስከ መጨረሻው አለመቀበል እንደሆነ አምናለሁ (ዮሐ. 3:36)። የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ በቃሉ አማካኝነት ስለሚመሰክር፥ ኃጢአተኞች ያንን ምስክርነት እምቢ ብለው መንፈስ ቅዱስን መቃወም ይችላሉ። ሆኖም፥ መንፈስ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ይመሰክራል (ዮሐ. 16:7-15)፤ ስለሆነም ሰዎች መንፈስ ቅዱስን የሚያስተናግዱበት መንገድ የእግዚአብሔርን ልጅ የሚያስተናግዱበት መንገድ ነው።

## 2. ከምኞት ተጠንቀቁ (12:13-21)።

በዚህ ጊዜ ከሕዝቡ መካከል አንዱ ኢየሱስን አቋረጠውና የቤተሰብን ችግር እንዲያቃልል ጠየቀው። የአይሁድ ምሁራን (ራቢዎች) ሕጋዊ ጉዳዮችን ለማስተካከል እገዛ እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸው ቢሆንም፥ ኢየሱስ ግን ሊሳተፍ አልፈለገም። ለምን? ምክንያቱም እርሱ የሚሰጠው መልስ እውነተኛውን ችግር ማለትም በሁለቱ ወንድማማቾች መካከል ያለውን ምኞት እንደማይፈታ ያውቅ ነበር። ሁለቱም ሰዎች ስግብግቦች እስከሆኑ ድረስ የትኛውም መፍትሔ ፈጽሞ ሊያረካቸው አይችልም። እጅግ የሚያስፈልጋቸው

ነገር ቢኖር የልባቸው መለወጥ ነው። ዛሬ እንደምናያቸው እጅግ ብዙ ሰዎች እነዚህም ኢየሱስ እንዲያገለግላቸው እንጂ እንዲያድናቸው አልፈለጉም ነበር።

ምኞት ካገኘነው በትክክል እንረካለን ብለን ለምናስበው ነገር የሚኖረን የማያቋርጥ ጥማት ነው። ይህም ለገንዘብ ወይም ገንዘብ ሊገዛቸው ለሚችላቸው ነገሮች፥ ወይም ለሥልጣንና ኃይል የሚኖረን ጉጉት ሊሆን ይችላል። ኢየሱስ እውነተኛ ሕይወት በሀብት ላይ እንደማትደገፍ በግልጽ ተናግሯል። የተወሰኑ መሠረታዊ ፍላጐቶች እንዳሉን ግን አልካደም (ማቴ. 6፡32፤ 1ኛ ጢሞ. 6፡17)። እርሱ የሚለው እነዚህን ነገሮች በማብዛት ሕይወትን ልናረካት እንደማንችል ነው።

አንድ ጊዜ ማርክ ትዌይን ለሥልጣኔ «የማያስፈልጉንን ያለልክ ማግበስበስ» የሚል ፍች ሰጥቶ ነበር፤ ይህም ትክክል ነበር። እንዲያውም፥ አላወቁም እንጂ በምኞት የተበከሉት ክርስቲያኖች ብዙ ናቸው። በ1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 6 ውስጥ ጳውሎስ የሰጠው ምክር ለ«ሀብታሞችና ዝነኞች» ብቻ የሚሠራ ይመስላቸዋል።

ኢየሱስ ይህንን ምሳሌ የተናገረው በሚመኝ ልብ ውስጥ ያለውን አደገኛ ነገር ለመግለጽ ነው። ከፍሉን ስታነብ ለተጠቃሹ ገበሬ ልዩ ልዩ ልምምዶች የራስህን ምላሾች አነጻጽር።

ለሀብታሙ ገበሬ ማመንታት ምን ምላሽ ትሰጣለህ? በዚህ ክፍል እጅግ ብዙ ሀብት በማግኘቱ የተቸገረውን ገበሬ እናገኛለን። «ኖሮኝ በቸገረኝ?» የምንል ከሆነ፥ ምናልባትም ምኞት በልባችን ነግሦ አል ማለት ነው። እጅግ የበረከተ ገንዘብ በውርስ ብታገኝ ይኼ ችግር ይፈጥርብህ ይሆን? ወይስ ዝም ብለህ እግዚአብሔርን ካመሰገንህ በኋላ ምን እንድታደርግበት እንደሚፈልግ ትጠይቀዋለህ?

ብልጽግና አደጋዎች አሉት (ምሳ. 30፡7–9)። ሀብት የእግዚአብሔርን ቃል ሊያንቅ (ማቴ. 13፡22)፥ ወጥመዶችንና ፈተናዎችን ሊፈጥር (1ኛ ጢሞ. 6፡6–10፥ 17–19) እና የአታላይ ዋስትና ሊሰጥህ ይችላል። ሰዎች ገንዘብ አያረካም ይላሉ፤ ዳሩ ግን ባለህ ለመኖር ከፈለግህ በደንብ ያረካል። ገንዘብ ሊገዛቸው በሚችላቸው ነገሮች ብቻ የሚረኩ ሰዎች፥ ገንዘብ ሊገዛቸው የማይችላቸውን ነገሮች በማጣት ከፍተኛ አደጋ የተከበቡ ናቸው።

ይህ ገበሬ ሀብቱን የተመለከተው ራሱን የሚያረካበት መልካም ዕድል አድርጎ ነው። ስለ ሌሎች ወይም ስለ እግዚአብሔር ምንም አላሰበም።

ለሀብታሙ ሰውዬ ውሳኔዎች ምን ምላሽ ትሰጣለህ? «ይኼ መቼም ማለፍያ ትርፍ ነው! ገንዘቡን አስቀምጥና ለወደፊት ተጠቀምበት!» ትል ይሆን? ኢየሱስ ግን ይኼ ሰውዬ ባደረገው ነገር ሁሉ ስግብግብነትን ያህል (የተጠቀማቸውን አያሌ ተውላጠ ስሞች ተመልከት)፥ ሰውዬውም ሞኝ እንደሆነ ተናግሯል። የዓለም ፍልስፍና «ለቀዳሚው ነገር እኔን ተጠንቀቅ!» የሚል ሲሆን፥ ኢየሱስ ግን ለዚህ ፍልስፍና ስፍራ አልሰጠም።

ጥሩ የሥራ መመሪያ መከተሉም ሆነ ለወደፊት ማጠራቀሙ በራሱ ስሕተት አይደለም (1ኛ ጢሞ 5፡8)። ኢየሱስ የንብረትን በከንቱ መባከን አይደግፍም (ዮሐ. 6፡12)። እንዲሁም በምኞት አነሣሽነት የሚከናወነውን ራስ–ወዳድነት አይደግፍም።

ለገበሬው ፍላጎቶች ምን መልስ ትሰጣለህ? «ሕይወት ማለት ይኼ ነው! ሰውየው ስኬት፥ እርካታና ዋስትና አግኝቷል! እንግዲህ ምንም አያሻውም!» ትል ይሆን? ኢየሱስ ግን ይህንን ሰውዬ የተመለከተው በሕይወቱ ደስ ሲሰኝ ሳይሆን፥ ሞትን ሲጋፈጥ ነው። የመሞቻ ጊዜያችን ሲደርስ ሀብታችን ከሞት አያድነንም፤ ወይም እግዚአብሔርንና ሌሎችን ገለል አድርገን ስለ ራሳችን ብቻ ስናስብ ያመለጡንን መልካም ዕድሎች ገዝቶ አያመጣልንም።

ኢየሱስ እውነተኛ ሕይወት ከነገሮች መብዛት እንደማይመጣ በግልጽ ተናግሯል፤ እውነተኛ ስኬት ወይም ዋስትናም እንዲሁ። ይህ ሰው ለሞትም ሆነ ለሕይወት የተሳሳተ አመለካከት አለው። ሕይወት ሀብትን ከማከማቸት እንደሚገኝና ሞትም ሩቅ እንደሆነ ያስብ ነበር። መጋቢት 11/1856 (እ.ኤ.አ) ሄንሪ ዴቪድ ተሮ በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ፥ «ብዙ ፍላጎት የሌለው ሰው ሀብታም ነው፤ የአንድ ሰው ሀብት የሚለካው እርሱን በሕይወት ለማኖር የሚያስችሉትን ነገሮች ለመግዛት ካለው ዓቅም አንጻር ነው» ሲሉ ጽፈው ነበር።

በመጨረሻም፥ ለትምክሕተኛው ገበሬ አሟሟት ምን ምላሽ ትሰጣለህ? «ሁሉም ነገር እየተሳካለት ሲሄድ መሞቱ የሚያሳዝን ነው! ታላላቅ ዕቅዶቹን ለመፈጸም አለመቻሉ ምንኛ አሳዛኝ ነገር ነው!» ወደ ማለቱ እናዘነብላለን። ይሁንና፥ ከሁሉም የከፋው አሳዛኝ ነገር ጥሎ የሄደው ሳይሆን ከፊቱ የሚጠብቀው ነው፤ ይኸውም ለዘላለም

ከእግዚአብሔር መለየቱ ነው። ሰውዬው ያለ እግዚአብሔር ኖሮ ያለ እግዚአብሔር ሞተ፤ ሀብቱ በሕይወቱ ውስጥ የተከሰተ ነገር ብቻ ነው። እግዚአብሔር በገንዘባችን አይደሰትም።

«በእግዚአብሔር ዘንድ ባለ ጠጋ መሆን» ምንድን ነው? ያለን ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣ በማመን እርሱን ማመስገንና እርሱ የሚሰጠንን ነገር ሁሉ ለሌሎች በሚበጅና ለእግዚአብሔር ክብር በሚውል መንገድ ለመጠቀም መጣር ማለት ነው። ዓላማችን እግዚአብሔርን ማስከበር ከሆነ፥ ሀብት አስደሳችና ለመልካም ተግባር የሚውል ነገር ሊሆን ይችላል (1ኛ ጢሞ. 6፥ከ10 ጀምሮ)። በእግዚአብሔር ዘንድ ባለጠጋ መሆን ማለት የግል ደስታ ብቻ ሳይሆን፥ መንፈሳዊ ብልጽግና ነው። ሰዎች በዚህ ዓለም ሀብት አካብተው በቀጣዩ ዓለም መደህየታቸው ምንኛ የሚያሳዝን ነገር ነው! (ማቴ. 6፡19–34 ተመልከት።)

## 3. ከመጨነቅ ተጠንቀቁ (12፡22–34)።

ሀብታሙ ሰውዬ የተጨነቀው እጅግ ብዙ ገንዘብ ስለነበረው ሲሆን፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን በቂ ገንዘብ ስላልነበራቸው በጭንቀት ሊፈተኑ ይችሉ ነበር። ክርስቶስን ለመከተል ሲሉ ያላቸውን ሁሉ የተው ሲሆን፥ ውልም ሆነ ዋስትና አልነበራቸውም። የሚኖሩት በእምነት እንደመሆኑ፥ እምነታቸውም ሁል ጊዜ ይፈተን ነበር።

ጭንቀት ጐጂ ነው። በቁጥር 22 «አትጨነቁ» ተብሎ የተተረጐመው ቃል «ውሳኔ ለመስጠት እየተሳነው የሚያወላውለውን እና የሚተክዘውን» ሰው ያመለክታል፤ «አታወላውሉ» (ቁጥር 29) የሚለው ደግሞ «ምን ይመጣ ይሆን? እያላችሁ አንዴ ወዲያ አንዴ ወዲህ አትበሉ» የሚል ፍች አለው። ይህ በማዕበል የሚናወጥ መርከብ ተምሳሌት ነው። ኮሬ ቴን ቡም፥ «ጭንቀት የዛሬን ጉልበት ያራቁታል እንጂ የነገን ኃዘን አይቀንሰውም» ይሉ ነበር።

በተጨማሪም፥ ጭንቀት የሕይወትን፥ የራሱንና የእግዚአብሔርን የተሳሳተ ገጽታ ስለሚያሳየን አታላይ ነው። ጭንቀት ሕይወት በምንበላውና በምንለብሰው ነገር እንደተዋቀረ አድርገን እንድናምን ያደርገናል። እኛም ያንኑ ስለማግኘት እያሰላሰልን ዳር በሚያደርሰን በፍጻሜው ቁም–ነገር ላይ ምንም ዓይነት አሳብ አይኖረንም፤ ይኸውም እግዚአብሔርን ማስከበሩ ላይ ነው (ማቴ. 6፡33)። ኑሮን በማደራጀትና ሕይወትን በማትረፍ መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ።

ጭንቀት በአካባቢያችን ያለውን ሕዝብና እግዚአብሔር ለፍጥረቱ የሚጠነቀቅበትን መንገድ ስለመመልከት ዕውር ያደርገናል። እግዚአብሔር አበቦችን ሲያስውብ፥ ለመዝራትም ሆነ ለማጨድ የማይችሉትን ወፎች ይመግባል። ስለሆነም የመሥራትን ብቃት ለሰጣቸው ሰዎችም እንክብካቤ ማድረግ መቻል አለበት። ኢየሱስ ቁጭ ብለን እግዚአብሔር እንደሚመግበን እየተናገረ አልነበረም፤ ወፎችም ራሳቸው በሕይወት ለመቆየት ተግተው ይሠራሉና። ይልቁንም፥ እርሱ የሚሰጠንን ችሎታዎችና ዕድሎች በመጠቀም በእርሱ እንድንታመን ከእርሱ ጋር እንድንተባበር ያበረታታናል (2ኛ ተሰ. 3፡6–15)።

ጭንቀት ግን ያሳውረናል። ከመጨነቅ የተነሣ በሕይወታችን መልካም ነገሮች ይፈጽሙልናል ብለን ወደ ምናስብበት ስፍራ ልንደርስ እንችላለን። በቁጥር 25፥ ጌታችን ጭንቀታችን ዕድሜያችንን ለአንድ ደቂቃ እንኳ እንደማያስረዝም [መዝ. (39)፡5] ወይም በቁመታችን ላይ አንድ ክንድ እንደማይጨምር ተናግሯል። የባለጸጋው ሰውዬ ጭንቀት ዕድሜውን አላስረዘመለትም! ጭንቀት በሕይወታችን ላይ በመጨመር ፋንታ ከሕይወታችን ይቀንሳል። የሰዎች ጭንቀት ወደ ሕመም ወይም ወደ ሞት ሊመራቸው ይችላል።

አሁንም ኢየሱስ ከዝቅተኛው ነጥብ ወደ ከፍተኛው እየተሻገረ አሳቡን ይገልጻል። እግዚአብሔር ወፎችን የሚመግብ ከሆነ ልጆቹን እንደሚመግብ ጥርጥር የለውም። ዛሬ በቅለው ነገ የሚረግፉትን ተክሎች የሚያሣምር ከሆነ፥ የራሱንም ሕዝብ እንደሚያለብስ ጥርጥር የለውም። እርሱ ማንኛውንም ነገር ሊያደርግ ስለሚችል ችግሩ የእርሱ ኃይል ከማነሱ ላይ አይደለም፤ የእኛ እምነት ከመጉደሉ ላይ እንጂ!

ጭንቀት <u>ጉዶሎዎች</u> ያደርገናል፤ ዕድገታችንን በማቀጨጭ በዓለም እንደሚገኙ ያልዳኑ ሰዎች ያደርገናል (ቁጥር 30)። በአጭሩ ጭንቀት የክርስቲያን ባሕርይ አይደለም፤ ጭንቀት ኃጢአት ነው። እኛ ራሳችን እግዚአብሔርን በመጠራጠር የምንጨነቅ ከሆነ፥ ከደኅንነት ርቆ ለጠፋው ዓለም ልንመሰክርና እምነታቸውን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እንዲያደርጉ እንዴት ልናበረታታቸው እንችላለን? እምነትን እየሰበኩ በእምነት አለመኖሩ የተፋለሰ አካሄድ አይደለምን? የቀድሞው የዩናይትድ ስቴትስ ሴኔት ቻፕሌይን (የሃይማኖት ጉዳዮች አስፈጻሚ ፒተር ማርሻል በአንድ ወቅት፥ «የጨጓራ በሽታ የእምነታችን ምልክት እንዳይሆን» ጸልየው ነበር። ብዙውን ጊዜ ግን የጨጓራ በሽታ የእምነታችን ምልክት ሆኖ ይታያል።

ጭንቀትን እንዴት እናስወግድ? የመጀመሪያው እርምጃ እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን እንደሚያውቅና እንደሚሞላልንም ልንታመንበት እንደምንችል ማወቅ ነው። እኛ በአነስተኛ መንጋው ውስጥ የምንገኝ በጎች፥ በቤተሰቡ ውስጥ ያለን ልጆችና የመንግሥቱ ሠራተኞች ነን፤ ስለሆነም ጉድለቶቻችንን ሙሉ ለሙሉ እንደሚሞላ ጥርጥር የለውም። መንግሥቱን ሊሰጠን ከወደደ፥ የሚያስፈልገንን ሁሉ አይሰጠንም ይሆን? (ሮሜ 8:32 ተመልከት።)

ይሁንና፥ የእግዚአብሔር ደስታና የእኛ ሀብት አብረው ሊጓዙ ይገባል። ምድርን በሰማያዊ የእይታ መነጽር ልንመለከትና የእግዚአብሔርን መንግሥት ከሁሉም ልናስቀድም ይገባል። ዋንኛው ጥያቄ፥ «ልብህ የት ነው?» የሚለው ይሆናል። ልባችን ጊዜያዊና ምድራዊ በሆኑት ነገሮች ላይ ካረፈ ሁልጊዜም ከጭንቀት አንወጣም። ዳሩ ግን ልባችን በዘላለማዊ ነገሮች ላይ ከተጣበቀ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችንንና አሳባችንን ይጠብቃል (ፊልጵ. 4:6-9)። በዚህ ዓለም ሀብቶች ላይ ሳናተኩር፥ ሌሎችን ለመርዳት ያለንን ለመሸጥ እንኳ ፈቃደኞች ልንሆን ይገባል (የሐዋ. 2:44-45፤4:34፤35)። መልሰው እኛኑ እስካልገዙን ድረስ ንብረቶች ማፍራታችን ስሕተት አይደለም።

## 4. ከግዴለሽነት ተጠንቀቁ (12:35-53)።

ኢየሱስ አትኩሮቱን ስለ አሁኑ ጊዜ ከመጨነቅ በወደፊቱ ጉዳይ ላይ ወደ መጠንቀቁ አሻግሯል። የሉቃስ ምዕራፍ 12 ጭብጦች ሁሉ በአንድነት ይጓዛሉ፤ ምክንያቱም ግብዝነትን፥ ምኞትንና ጭንቀትን ለማሸነፍ ከሁሉም የሚሻለው መንገድ የጌታን ምጽአት ወደ ፊት አሻግሮ መመልከት በመሆኑ ነው። በወደፊት የጊዜ ሠሌዳ መሠረት በምትኖርበት ጊዜ፥ የዓለም ነገሮች ሊያጠምዱህ ይቸገራሉ። በዚህ ክፍል ኢየሱስ ለምጽአቱ እንዴት እንደምንዘጋጅ ገልጾአል።

<u>መጠባበቅና መንቃት</u> (ቁጥር 35-40)። የአይሁድ ሰርጎች የሚካሄዱት በምሽት ሲሆን፥ የሙሽራው አገልጋዮች ጌታቸው ሙሽራዪቱን ይዞ እስኪመለስ ድረስ ይጠባበቁ ነበር። በመሠረቱ፥ አዲስ ባል አገልጋዮች ከበር ላይ ቆመው እርሱንና ሙሽራይቱን እንዲጠብቁ አይፈልግም። ዳሩ ግን አገልጋዮች እንደ ልባቸው ለመንቀሳቀስ እንዲችሉ ወገባቸውን ታጥቀው ለሥራ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል (1ኛ ጴጥ. 1:ከ13 ጀምሮ)።

በዚህ ታሪክ ውስጥ አስደናቂው ነገር ጌታው አገልጋዮቹን ማገልገሉ ነው። በአይሁድ ሰርጎች፥ ሙሽራዪቱ እንደ ንግሥት ሙሽራው

ደግሞ እንደ ንጉሥ ይስተናገዱ ነበር፤ ስለሆነም «ንጉሡ» ለአገልጋዮቹ አገልግሎት እንዲሰጥ አይጠበቅበትም። ንጉሣችን በሚመለስበት ጊዜ ታማኝ አገልጋዮቹን ከማገልገሉም በላይ ለታማኝነታችን ይሸልመናል።

«መንቃት» ማለት መዘጋጀትና አለመዘናጋት ማለት ነው። የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምጽአት በተመለከተ ይህንኑ ልናደርግ ይገባል። የእርሱ አመጣጥ እንደ ሌባ ነው። አዋጅ ሳያስነግርና ሰዎችም ሳይጠብቁት ከተፍ ይላል (1ኛ ተሰ. 5፡2፤ ማቴ. 24፡43፤ ራእ. 16፡15)። ዝግጁ ልንሆን ይገባል!

የፕሪስቢቴርያን ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የነበሩት ሮበርት ሙሬይ ማክቼን አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን፥ «ዛሬ ኢየሱስ ይመጣል ብለህ ታምናለህ?» ብለው ይጠይቁ ነበር። አሉታዊ ምላሽ ለሚሰጡትም፥ «እንግዲህ ብትዘጋጅ ይሻልሃል፤ እርሱ አንተ በማታስብበት ሰዓት ይመጣልና!» ይሉ ነበር።

<u>መሥራት</u> (ቁጥር 41-48)። የሚያስፈልገን ነገር ቢኖር መጠባበቅና መንቃት ብቻ እንደሆነ ማሰብ ስለሌለብን ኢየሱስ በሚመጣበት ጊዜ በሥራ ላይ እንድንሆን ለማበረታታት ይህንን ምሳሌ ሰጥቷል። ሐዋርያት የእግዚአብሔር ቤት የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን የመመገብ ኃላፊነት ነበራቸው፤ እያንዳንዳችን ደግሞ በዚህ ዓለም ውስጥ እንፈጽመው ዘንድ ጌታ የሰጠን ሥራ አለን። ኃላፊነታችን እርሱ ሲመጣ ታማኝ ሆኖ መገኘት ነው። በራሳችን ወይም በሌሎች ሰዎች ዓይን ሲታይ ያልተሳካልን መስለን ልንታይ እንችላለን። ያ ግን አስፈላጊው ነገር አይደለም። እግዚአብሔር የሚፈልገው ታማኝነትን ነው (1ኛ ቆሮ. 4፡2)።

አማኝ ጌታው ተመልሶ እንደማይመጣ ማሰብ ከጀመረ፥ ሕይወቱ ሊበላሽ ይጀምራል። ከሌሎች ጋር ያለን ግንኙነት ከጌታ ጋር ባለን ግንኙነት ላይ ይመሠረታል፤ ስለሆነም እርሱን መጠባበቅ ካቆምን የእርሱንም ሰዎች ከመውደድ እንታቀባለን። ለክርስትና ሕይወትና አገልግሎት የሚያነሣሣን ጌታን የማስደሰትና በሚመለስበትም ጊዜ ታማኝ ሆኖ የመገኘቱ መሻት ሊሆን ይገባል።

ወደ መንግሥተ ሰማይ የመግባታችን ጉዳይ የተመሠረተው በሠናይ ምግባራችን ላይ ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናችን ላይ ስለሆነ፥ ቁጥር 46 ያልታመኑ አማኞች ደኅንነታቸውን እንደሚያጡ የሚያስተምር አይመስለኝም (ኤፌ. 2፡8-10፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡11-13)። «ከሁለት ይሰነጥቀዋል» የሚለው «ይለየዋል፥ ያስወግደዋል» የሚል ፍች አለው። ጌታችን ታማኝ አማኞችን ከማይታመኑት ይለያል፤

ለታማኞቹ ሽልማት የሚሰጥ ሲሆን፥ ያልታመኑት ግን ሽልማታቸውን ያጣሉ (1ኛ ቆሮ. 3፡13–15)።

የእግዚአብሔር ፍርድ ያለአድልዎ በቅንነት የሚሰጥ ነው። ይህም ባሪያዎቹ ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ በሚያውቁት ነገር ላይ የሚመሠረት ይሆናል። ይህን ስንል ግን ብዙ ባላወቅን ቁጥር በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት የቀለለ ዳኝነት ይጠብቀናል ለማለት አይደለም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድናውቅ (ሮሜ 12፡2፤ ቈላ. 1፡9) እና ለኢየሱስ ክርስቶስ ባለን እውቀት እንድናድግ ምክር ተሰጥቶናል (2ኛ ጴጥ. 3፡18)። ኢየሱስ አጠቃላይ መመሪያ እየሰጠ ነው፤ ይኸውም ከእግዚአብሔር ዘንድ ብዙ እውቀት በተቀበልን መጠን፥ በፊቱ የሚኖረን ተጠያቂነት እንደሚከብድ ነው።

<u>መዋጋት</u> (ቁጥር 49–53)። ስንጠባበቅ፥ ስንነቃና ስንሠራ ሳለን በጠላት ግዛት ውስጥ እንደ መኖራችን መጠን ሁኔታዎች በቀላሉ የምንዘልቃቸው አይሆኑም። ኢየሱስ የተጠቀማቸው ተምሳሌቶች– እሳት፥ ጥምቀት፥ ክፍፍል– ስለ ተቃውሞና ግጭት ይናገራሉ። ለአይሁዶች እሳት የፍርድ ተምሳሌት ነበር፤ የጌታችንም ወደዚህ ዓለም መምጣት በትክክል ፍርድን አምጥቷል (ዮሐ. 9፡39–41)።

በቁጥር 50 የጌታችን «ጥምቀት» መከራውንና ሞቱን ያመለክታል፤ ይህም በዮርዳኖስ ወንዝ በመጠመቁ ተገልጾአል። [መዝሙር (42)፡7 እና ዮናስ 2፡3 ተመልከት፤ እንዲሁም በሉቃስ 11፡29–30 ስለ ዮናስ የተናገረውን አስብ።] ሐዋርያት ከበዓለ ኀምሳ በኋላ ለክርስቶስ ሲመሰክሩ የመከራ ጥምቀት ተቀብለዋል።

ሉቃስ መጽሐፉን የጀመረው «ሰላም በምድር» በሚል እወጃ ሲሆን (2፡14)፥ በዚህ ስፍራ ጌታ ከተስፋ ቃሉ ጋር የሚቃረን ይመስላል። ኢየሱስ በእርሱ ለሚያምኑት ሰላም ይሰጣል (ሮሜ 5፡1)፤ ዳሩ ግን ብዙውን ጊዜ የእምነት ምስክርነታቸው በቤተሰቦቻቸውና በጓደኞቻቸው መካከል የጦርነት እወጃ ይሆናል። ኢየሱስ የክፍፍል መንስዔ ነው (ዮሐ. 7፡12፥43፤9፡16፤10፡19 ተመልከት)። ይሁንና፥ በምድር ላይ ሰላም ባይገኝ እንኳ፥ በመስቀል ላይ በተፈጸመው የኢየሱስ ክርስቶስ *ሥራ* ምክንያት በሰማይ ሰላም አለ (19፡38)።

ደቀ መዛሙርቱን ካስተማረ በኋላ፥ ኢየሱስ ዞር ብሎ በዙሪያው ለነበሩት ሰዎች የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሰጣቸው።

5. ከመንፈሳዊ ድንዛዜ ተጠንቀቁ (12፡54-59)።

ኢየሱስ መንፈሳዊ ጉዳዮችን የመመርመርንና ጥንቃቄ የተሞላበት አሠራርን አስፈላጊነት ለሕዝቡ ለማስረዳት ሁለት ማብራሪያዎችን ተጠቅሟል። በመጀመሪያ ስለ አየር ንብረት፥ ከዚያ በኋላ ደግሞ ስለ ፍርድ ተናግሯል።

ምርመራ (ቁጥር 54-57)። ሰዎች ስለ አየር የሚመራመሩትን ያህል ጊዜ ለመንፈሳዊ ነገሮች ቢያውሉ ይሻላቸው ነበር። ሕዝቡ የዓውሎ ነፋስን መምጣት ለመተንበይ ሲችል፥ የሚመጣውን ፍርድ ግን እንደሚመጣ ለማየት አይችልም ነበር። የሙቀቱ መጠን ሊለወጥ እንደተቃረበ ሲያውቅ፥ «የዘመኑን ምልክቶች» ለመተርጐም አይችልም ነበር። የአይሁድ ሕዝብ ለብዙ ምእተ ዓመታት የትንቢት መጻሕፍት የነበሩዋቸው በመሆኑ፥ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ነገር ማወቅ ነበረባቸው፤ ዳሩ ግን ሃይማኖታዊ መሪዎቻቸው ወደ ጥፋት መሯቸው።

ዛሬ ሰዎች የሰማያዊ አካላትን እንቅስቃሴ ሊተነብዩ፥ «አቶሞች»ን ሊሰነጣጥቁና ሰውን በጨረቃ ላይ ሊያስቀምጡ ችለዋል። እግዚአብሔር በምድራችን ላይ የሚያደርገውን ነገር ለማየት ዕውር መሆናቸው ግን ምንኛ አሳዛኝ ነው! ወደ ከዋክብት መሄዱን ሲያውቁ ወደ መንግሥተ ሰማያት ስለ መሄዱ ግን አያውቁም። የሠለጠነው ዓለማችን ብዙ የሳይንስ እውቀት ሲኖረው፥ መንፈሳዊ ጥበብ ይጐድለዋል።

ጥንቃቄ የተሞላበት አሠራር (ቁጥር 58-59)። ማንኛውም ሰው ወደ ወኅኒ ቤት ውስጥ ላለመግባት አስፈላጊውን ሁሉ ጥንቃቄ ያደርጋል፤ ዳሩ ግን ወደ ሲኦል ላለመውረድ በማሰብ የሚጠበቅባቸውን ጥንቃቄ የሚያደርጉ ስንት ሰዎች ናቸው? ጠበቆችና ዳኞች የሕግ መዝገባቸውን የሚያጠኑትን ያህል የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ ቢመረምሩ፥ ሕግ ሊሰጣቸው የማይችለውን ጥበብ ያገኙ ነበር።

እስራኤላውያን ወደ ፍርድ እየገሠገሡ ነበር፤ ፈራጁም ሁሉን ቻዩ አምላክ ሲሆን፥ የሰላምን መንገድ የሚፈልጉ አልነበሩም (13፡34-35)። ኢየሱስ የሮም ወታደሮች ቤተ መቅደሱንና ከተማዪቱን ለማውደም እንደሚመጡ ቢያውቅም (19፡41-44)፥ ሕዝቡ ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሊያሳምናቸው አልቻለም። የመጨረሻውን ሳንቲም ይከፍሉ ዘንድ ዕዳቸው የተራራን ያህል እያሻቀበ ሄዶአልና።

እነዚህን እውነቶች ከግል ሕይወታችን ጋር ልናዛምድ እንችላለን። የዐውሎ ነፋሱን መምጣት ካወቅን ዝግጅት እናደርጋለን። አንድ ባለሥልጣን ወደ ፍርድ ቤት ሊወስደን እንደሚመጣ ከሰማን፥ ጠበቃ እንፈልግና ጉዳዩን ከችሎት ውጭ ለመጨረስ እንሞክራለን። የእግዚአብሔር ፍርድ ዐውሎ ነፋስ እየመጣ ሲሆን፥ ዳኛውም ቀደም ብሎ ከበሩ ላይ ቆሟል (ያዕ. 5:9)።

«እነሆ፥ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው፤ እነሆ፥ የመዳን ቀን አሁን ነው» (2ኛ ቆሮ. 6:2)።

## – 12 –

# ጥያቄዎችና መልሶች

### ሉቃስ 13

አንድ አይሁዳዊ ተማሪ መምህሩን፥ «ረቢ ሆይ፥ ለምንድን ነው ጥያቄ በምጠይቅዎ ጊዜ እርስዎ ሁልጊዜ ሌላ ጥያቄ በመጠየቅ መልስ የሚሰጡኝ?» ሲል ጠየቃቸው።

ረቢውም፥ «ለምን አልጠይቅህም?» ሲሉ አሁንም ጥያቄ አስከተሉበት።

ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም መጓዝ በጀመረ ጊዜ፥ ምላሽ የሚያሻቸውን ጥያቄዎች ያካተቱ አራት ሁኔታዎች አጋጠሙት። የጀርመናውያኑ ምሳሌያዊ አነጋገር፥ «አንድን አዋቂ ሰው መጠየቅ የጥበብ መጀመሪያ ነው» ይላል። ይሁንና፥ ኢየሱስን የጠየቀው ሁሉ ጥያቄውን ያነሣው ከትክክለኛ ዓላማ በመነሣት አልነበረም፤ ይህም ቢሆን ኢየሱስ ማወቅ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንዳናስተምር አላቆመውም። በሉቃስ 13 የሚገኙትን የኢየሱስን መልሶች በምታጠናበት ጊዜ፥ ስለ እርሱና ስለ አገልግሎቱ የበለጠ ታውቃለህ፤ እንዲያውም በክርስትና ሕይወት እርሱን ለማስደሰት የሚቻልበትንም አኗኗር ትገነዘባለህ።

## 1. ስለ ፍትሕ የቀረበ የፖለቲካ ጥያቄ (13፡1–9)።

ለሃይማኖታዊ መረዳታቸው ግድ ስላልነበረው የሮማው አገረ ገዥ ጴንጤናዊው ጲላጦስ ከአይሁዶች ጋር አይስማማም ነበር። ለምሳሌ፥ የንጉሡ ምስል ያለበትን የሮም መንግሥታዊ ባንዲራ ወደ ኢየሩሳሌም በማምጣት፥ የቄሣር ምስል በቅድስቲቱ ከተማ ውስጥ እንዲሰቀል የማይፈልጉትን አይሁዶች አስቆጥቷል። ጲላጦስ ተቃዋሚዎቹን ለመግደል የዛተ ሲሆን፥ እነርሱም ለመሞት ፈቃደኞች ነበሩ። ቆራጥነታቸውን በመመልከቱ ንጉሡ የቄሣርን ምስሎች ወደ ቂሣርያ መለሳቸው፤ ያ ግን ጠላትነቱን ሊያበርድ አልቻለም።

በቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰው ግድያ የተፈጸመው ምናልባትም ጲላጦስ የውኃ ቧንቧውን ሥራ ለማካሄድ የመቅደሱን ገንዘብ በወሰደ ጊዜ ይሆናል። በዚህ ጊዜ የተቆጡ አይሁዶች የተከማቹበት ቡድን ለተቃውሞ ተሰበሰበ፤ የጲላጦስም ወታደሮች ወታደራዊ ልብሳቸውን ቀይረው እንደ ተራ ሰው በሁከቱ መካከል ተደባለቁ። ከዚያም

ወታደሮቹ ደብቀው የያዙአቸውን መሣሪያዎች አውጥተው ንጹሕና መሣሪያ የሌላቸው አይሁዳውያንን ገደሉ፤ ይህም አይሁዶች በገዢያቸው ላይ ያላቸውን ጥላቻ ከመጨመር በቀር ያበረከተው አስተዋጽኦ አልነበረም።

ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሊሄድ ስለተነሣ፥ የሚናገረው ማንኛውም ነገር ከእርሱ ቀድሞ ጲላጦስ ዘንድ እንደሚደርስ የታወቀ ነበር። ጉዳዩን ችል ብሎ ቢያልፍ፥ ሕዝቡ ሮማውያንን እንደሚደግፍና ለወገኖቹ ታማኝ እንዳልሆነ አድርገው ይከሱት ነበር። ለአይሁዶች በመቆም ጲላጦስን ቢቃወም ደግሞ ከሮማውያን ጋር ይጋጭና አይሁዶችም እርሱን ለማሳሰር ጥሩ ማመኻኛ ያገኙ ነበር።

ጌታችን የተነሣውን ጉዳይ በከፍተኛ ትኩረት በመመልከት የፖለቲካውን ጥያቄ ጭራሽ አገለለው። ስለ ጲላጦስ ኃጢአቶች ከመናገር ይልቅ፥ እርሱን ስለሚጠይቁ ሰዎች ኃጢአት ይናገር ጀመር። ጥያቄያቸውን በጥያቄ መለሰላቸው!

በመጀመሪያ ደረጃ፥ በሰው ልጅ ላይ የሚደርሱ አሳዛኝ ሁኔታዎች ሁልጊዜም መለኮታዊ ቅጣቶች እንዳልሆኑና «እንደ እግዚአብሔር በመሆን» ፍርድ መስጠቱ ተገቢ እንዳልሆነ ገለጸ። የኢዮብ ጓደኞች የኢዮብ መከራዎች የኃጢአተኝነቱ መረጃዎች እንደሆኑ በመናገራቸው ይህንኑ ስሕተት ፈጽመዋል። መከራን በተመለከተ የዚህ ዓይነቱን አቋም የምንይዝ ከሆነ፥ የሐዋርያትን፥ የነቢያትንና የጌታችንም መከራዎች ለማብራራት እንቸገራለን።

«የሰሊሆም ግንብ ወድቆ የገደላቸውን ሰዎች አሟሟት እንዴት ትገልጹታላችሁ? ያ የጲላጦስ ጥፋት አልነበረም። የእግዚአብሔር ጥፋት ነበርን? እርሱን እንውቀሰው? በሰሊሆም የተገደሉት አሥራ ስምንቱ ሰዎች የዕለት ተግባራቸውን በማከናወን ላይ ነበሩ፤ ይሁንና ሞቱ! ተቃውሞ እያሰሙ ወይም ችግር እየቆሰቆሱ አልነበሩም» ሲል አስረዳቸው።

ዓይነ-ስውሩ እንግሊዛዊ ገጣሚ ጆን ሚልተን እጅግ ባረጀበት ጊዜ ፕዩሪታኖች ራሱን ቆርጠው የገደሉት ንጉሥ ልጅ፥ ቻርልስ ዳግማዊ ጎብኝቶት ነበር። ንጉሡም፥ «ዓይነ-ስውርነትህ ከእግዚአብሔር የመጣ ፍርድ ነው፤ ይህም የሆነው በአባቴ ላይ በተወሰደው የመግደል እርምጃ ላይ ተካፋይ ስለነበርህ ነው» አለው። ሚልተንም፥ «እኔ ዓይኔን ያጣሁት በእግዚአብሔር ፍርድ ከሆነ፥ አንገቱ ስለተቀነጠሰው አባትህ ምን ትላለህ?» ሲል መለሰለት።

ኢየሱስ የሙግታቸውን እውነተኛ መደምደሚያ ማሳየቱን ቀጠለ፤ ይኸውም እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን በራሱ መንገድ የሚቀጣቸው ከሆነ፥ ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ስለሆኑ እነርሱም ራሳቸው ንስሐ ቢገቡ እንደሚሻላቸው ነው። ወሳኙ ጥያቄ፥ «እነዚህ ሰዎች ለምን ሞቱ?» የሚለው ሳይሆን፥ «አንተስ ምን የመኖር መብት አለህ?» የሚል ነው። ከእኛ ኃጢአት ያልሠራ ስለሌለ፥ ሁላችንም ብንዘጋጅ መልካም ነውና።

ስለ ራሳችን ኃጢአትና ሞት ከመናገር ይልቅ ስለ ሌሎች ሰዎች ሞት መናገሩ ቀላል ነው። በአሜሪካ የኅትመት ሥራዎች ከፍተኛ ገቢ ያገኘ የነበረው ዊልያም ራንዶልፍ ሂርስት እርሱ ባለበት ስፍራ ማንም ስለሞት እንዲያወራ አይፈቀድም ነበር፤ ይህም ሆኖ፥ ከሞት አላመለጠም። አንድ ወዳጄን እርሱ በሚኖርበት ከተማ በየዓመቱ የሞቱት ስንት ያህል እንደሆኑ ጠየቅሁት፤ እርሱም፥ «አንድ በአንድ ይሞታሉ» ካለኝ በኋላ «ከዚህ በፊት ሞተው የማያውቁ ሰዎች እየሞቱ ናቸው» ሲል አከለልኝ።

እንደ ዘሌዋውያን 19፡23-25 አገላለጽ፥ ለመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት ከአዲስ ተክል የሚገኙ ፍሬዎች አይበሉም ነበር፤ የአራተኛው ዓመት ፍሬዎች ደግሞ ለጌታ ይሰጡ ነበር። አንድ ገበሬ እስከ አምስተኛው ዓመት ድረስ ምንም ዓይነት በለሶች ለራሱ አያገኝም ነበር፤ ይህ ሰው ግን ለሰባት ዓመታት ያህል ተጠባብቋል። ስለሆነም ፍሬ-አልባዋን ዛፍ ለመቁረጥ መሻቱ የሚያስደንቅ አይደለም!

ምሳሌው ከግለሰቦችና ከእስራኤል ሕዝብ ሕይወት ጋር ይዛመዳል። እግዚአብሔር ለሰዎች ቸርና ታጋሽ በመሆኑ (2ኛ ጴጥ. 3፡9)፥ ንስሐ ገብተን ፍሬ እንድናፈራ ለማበረታታት ከሚገባው በላይ ይተጋል (ማቴ. 3፡7-10)። ቆርጦ የመጣል ሙሉ መብት ቢኖረውም፥ በምሕረቱ አትርፎናል። ይህም ሆኖ፥ በመጨረሻው የፍርድ ቀን ስለሚመጣ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ትዕግሥት ማቃለል አይገባም።

በተጨማሪም፥ በለሲቱ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን ልዩ ቸርነት (ኢሳ. 5፡1-7፤ ሮሜ 9፡1-5) እና ያሳያቸውን ትዕግሥት ታስታውሰናለች። እግዚአብሔር ጌታችን በምድር ላይ ባገለገለባቸው ጊዜያት ለሦስት ዓመታት ቢጠባበቅም፥ ሕዝቡ ፍሬ አላፈራም። ከዚያም የሮም ሠራዊት ኢየሩሳሌምንና መቅደሷን እንዲያወድሙ ከመፍቀዱ በፊት ተጨማሪ አርባ ዓመታት ተጠባበቀ፤ በእነዚያ ዓመታት ቤተ ክርስቲያን ለሕዝቡ ስለ ወንጌል ከፍተኛ ምስክርነት ሰጠች። በመጨረሻም በለሲቱ ተቆርጣ ወደቀች።

አድማጮቹ መደምደሚያ ያበጁለት ዘንድ ምሳሌው ያለ ማስገንዘቢያ ክፍት ሆኖ መቅረቱ ጠቃሚ ነው (ትንቢተ ዮናስ ለዚህ ዓይነቱ ዘዴ ሌላው ምሳሌ ነው።) በለሲቱ ፍሬ አፍርታ ይሆን? የተደረገላት ልዩ እንክብካቤ ውጤት አስገኝቶ ይሆን? በለሲቱ ተረፈች ወይስ ተቆረጠች? ለእነዚህ ጥያቄዎች መልሶችን የምናውቅበት መንገድ የለንም፤ የራሳችንን ሕይወት በተመለከተ ግን ልንመልስ እንችላለን። አሁንም ጥያቄው፥ «የበለሲቱ ፍጻሜ ምን ሆነ?» የሚል አይደለም፤ «በእኔስ ላይ ምን ይደርስ ይሆን?» የሚያሰኝ እንጂ።

እግዚአብሔር ፍሬን ይፈልጋል። እርሱ ምንም ዓይነት ምትክ ስለማይቀበል፥ ንስሐ ለመግባት ጊዜው አሁን ነው። ወደፊት በብዙዎች ላይ ስለሚደርስ አሳዛኝ ሁኔታ ስትሰማ፥ «ዝም ብዬ ቦታ እያጣበብሁ ነው ወይስ ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆን ፍሬ እያፈራሁ ነኝ?» ብለህ ራስህን ጠይቅ።

## 2. ስለ ሰንበት የተነሣው ሕጋዊ ጥያቄ (13፡10–21)።

<u>ነፃነት</u> (ቁጥር 10–13)። «ለ18 ዓመታት ጐባጣ ሆኜ ብቆይ፥ ከሳምንት እስከ ሳምንት እግዚአብሔርን በምኵራብ ውስጥ በታማኝነት አመልከው ይሆን?» ብዬ አስባለሁ። ይህች ሴት እግዚአብሔር እንዲረዳት የጸለየች መሆኑ ባያጠራጥርም ገና አልተፈወሰችም። ይህም ሆኖ፥ እግዚአብሔር ለእርሷ የሚያስብ መስሎ መቆየቱ መራራ ወይም ጥላቻ የተሞላች እንድትሆን አላደረጋትም። እዚያው በምኵራብ ውስጥ ነበረች።

ሁልጊዜም ለሌሎች ሰዎች ጉድለት የሚያስብ እንደመሆኑ፥ ኢየሱስ ይህች ሴት ወደፊት እንድትመጣ ጠራት። ኢየሱስ ይህንን በማድረግ ለጉባኤው አካለ–ጐደሎነቷን ማሳየቱ ርኅራኄ የለሽ ድርጊት ቢመስልም (ማቴ. 12፡13 ተመልከት)፥ እርሱ የሚያደርገውን ያውቅ ነበር። ሰይጣንም በጉባኤው ውስጥ ስለነበረ፥ ኢየሱስ ሊያጋልጠውና ሊያሸንፈው ፈልጎአል። በተጨማሪም፥ ሴቲቱ ስለ ነፃነት ጠቃሚ ትምህርት እንዲያስተምር መነሻ ሆና እንድትረዳው ፈልጎ ነበር።

ሰዎችን የሚያጐብጥ ሰይጣን ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ኃጢአት [መዝ. (38)፡6]፥ ኃዘን [መዝ. (42)፡5] እና መከራም [መዝ. (44)፡25] ይህን ያደርጋሉ። እስረኛውን ነፃ ሊያወጣ የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ቃሉን ሲናገርና እጆቹን በእርሷ ላይ ሲጭን ተፈውሳ ለእግዚአብሔር ክብር ሰጠች! ያ ሕዝቡ እስከ መቼውም የማይረሱት የምኵራብ አገልግሎት ነበር።

ቁጣ (ቁጥር 14)። የምኵራብ አለቃው መደሰትና ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት ሲገባው እጅግ ተቆጣ (8፥41 ተመልከት)። በኢየሱስ ላይ ለመቆጣት ስላልደፈሩ ሕዝቡን ገሠጿቸው። ይሁንና፥ የቁጣ ንግግሩን ይበልጥ በተረዳህ መጠን፥ አስቂኝነቱም በደንብ ይገባሃል። ሰዎቹ በሽተኞቻቸው እንዲፈወሱ ቢያመጡ ማን ይፈውሳቸው? እርሱ የመፈወስ ኃይል ነበረው? ከነበረውስ ከዚህ በፊት ሰዎችን ለመርዳት ያልተጠቀመበት ለምንድን ነው? ሰውዬው ፈሪ፥ አልፎ ተርፎም ግብዝ ነበር።

የምኵራቡ አለቃው እስራት ከሴቲቱ የከፋ ነበር። የእርሷ እስራት የጐዳው ሰውነቷን ብቻ ሲሆን፥ የእርሱ ግን ልቡንና አእምሮውን ይዞበት ነበር። በወግ የታወረና የታሰረ በመሆኑ የእግዚአብሔርን ልጅ ተቃወመ! አልበርት ሑባርድ ወግ «ስንት ሰዓት እንደነበረ የሚነግረን አሮጌ መቁጠሪያ» እንደሆነ ተናግረዋል። የምኵራብ አለቃ «ይህን ዘመን» ሊመረምር ባለመቻሉ (12፥56) ለኩነኔ ተዳረገ።

ፍትሕ (ቁጥር 15-17)። ጌታ ይህችን ሴት በሌላ በማንኛውም ቀን ሊፈውሳት ይችል ነበር። ለአሥራ ስምንት የሥቃይ ዓመታት ታስራ የቆየች በመሆኑ አንድ ቀን ብትጨምር የጐላ ለውጥ አያመጣም። ይሁንና፥ ስለ ነፃነት ሊያስተምራቸው ስለፈለገ ሆነ ብሎ የሰንበትን ዕለት መረጠ። «መፈታት» የሚለውን ቃል መደጋገም ልብ ብለህ ተመልከት (ቁጥር 12፥15-16)።

በመጀመሪያ፥ ጌታ ለሴቲቱ ጥብቅና በመቆም የምኵራቡን አለቃ ገሠጸው። ኢየሱስ ይህ ሰው ለዚህች ሴት ካደረገላት መስተንግዶ ይልቅ ለቤት እንስሳት የሚያደርገው እንደሚበልጥ አስገነዘበው። ይህ ማስገንዘቢያ በጉባኤው ውስጥ የነበሩትን ሰዎችም ይጨምር ነበር። ጌታችን ከትንሹ ጀምሮ ታላላቅ የሚባሉትንም አሳብ እየሞገተ ነበር፤ ማለትም እግዚአብሔር ሰዎች የተጠሙ እንስሶቻቸውን በዕለተ ሰንበት እንዲረዱ ከፈቀደ፥ በራሱ አምሳል ለተፈጠሩት ድሆች እንክብካቤ እንድናደርግ አይፈልግም ይሆን? ሌሎችን ከመርዳት የሚያቅበን ማንኛውም ወግ ከእግዚአብሔር አይደለም። በርግጥ ወግን ምክንያት በማድረግ ሰዎችን አለመርዳት ቀላል ነው።

ኢየሱስ ሴቲቱ «የአብርሃም ልጅ» እንደሆነች ተናግሯል፤ ይህ መንፈሳዊ ሁኔታዋን እንጂ ሥጋዊ ውልደቷን የሚያመለክት አይደለም (ገላ. 3፥7፤ ሉቃ. 19፥9)። በዚያ የነበሩት የአይሁድ ሴቶች ሁሉ «የአብርሃም ልጆች» ነበሩ። ይህ ማለት ጌታ ሳይፈውሳት በፊት የተለወጠች አማኝ ነበረች ማለት ይሆን? ይህ ከሆነ ደግሞ በአዲስ

ኪዳን ውስጥ በአጋንንታዊ ጥቃት ሥጋዊ ጉዳት የደረሰባት ብቸኛ አማኝ ነበረች ማለት ነው። (በጳውሎስ ሥጋ ላይ የነበረው መውጊያ ምን እንደነበረ ወይም ሰይጣን ጳውሎስን ለመጕሰም እንዴት እንደተጠቀመበት የምናውቀው ነገር የለም። 2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 ተመልከት።)

ይህ የቃላት አመራረጥ ጉዳይ ሊሆን ቢችልም፥ በአማኞች ሕይወት ላይ የሚከሰተውን አጋንንታዊ ሥራ «በአጋንንት መያዝ» ከማለት «የአጋንንት ጫና» ማለቱ ይሻለኛል። እንዲያውም፥ የግሪኩ ቃል «አጋንንት ያደረበት» የሚል ፍች ስላለው «መያዝ»ን አጉልተን ልንመለከት አይገባም። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሕዝብ አእምሮና አካል እንደሚጎዳ ጥርጥር የለውም። አንዳንድ ሰይጣናዊ ጭቆና አንድ ሰው ሰይጣን ያመጣው መሆኑን እስኪያውቅ ድረስ ለብዙ ዓመታት ሊቆይ ይችላል። ሁሉም በሽታ ከአጋንንት ስለማይመጣ (6፡17–19)፥ ሁሉንም ነገር በሰይጣን ላይ ማላከክ የለብንም።

ከጉባኤው ውስጥ ሰንበትን በተመለከተ ኢየሱስን ለመክሰስ ተስፋ ያደረጉ ሰዎች ቢኖሩም፥ በሰጣቸው ምላሽ ስለ አፈሩ ምንም አልተናገሩም። ያስተላለፈው ትምህርት ግልጽ ነበር፤ ይኸውም ሰይጣን ሰዎችን በእስራት ውስጥ እንደሚያስቀምጥ ግን እውነተኛ ነፃነት የሚመጣው በክርስቶስ ከማመን መሆኑን ነው። እግዚአብሔር ለእኛ ሊሰጠን የፈለገው ሰንበት ወጐችን ከመጠበቅ የሚገኘውን ሳይሆን በጸጋው የሚታደለውን «የልብ ዕረፍት» ነው (ማቴ.11፡28–30)።

ከቁጥር 18–21 የሚገኙ ምሳሌዎች ለሕዝቡ የተነገሩት ምናልባትም ኢየሱስና አሥራ ሁለቱ ከምኩራብ ሊወጡ ሲሉ ይሆናል። እነዚህን ምሳሌዎች ከዚህ በፊት የተጠቀማቸው በመሆኑ ደቀ መዛሙርቱ ተረድተዋቸዋል (ማቴ. 13፡31–33፥51)። በእነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ አንዳንዶች የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚታይ ውጫዊ ዕድገት (የሰናፍጭ ዘር) መግለጫ እና የማይታይ ውስጣዊ ተጽዕኖ (እርሾ) አድርገው ይመለከታሉ። በእነዚህ ምሳሌዎች በመጠቀም ኢየሱስ፥ «እናንተ የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች ሙት ወጋችሁን እያጠበቃችሁ እውነቱን ትቃወሙ ይሆናል። ይሁንና፥ የእግዚአብሔር ሕያው መንግሥት አሁንም ታድጋለች። ሰይጣንም ይሸነፋል» እያለ ነበር።

ዳሩ ግን ሁለት ነገሮችን ልብ ማለት አለብን። በመጀመሪያ ደረጃ፥ ኢየሱስ ከዚህ በፊት እርሾን የክፉ ነገር ምሳሌ አድርጐ የተጠቀመ በመሆኑ (12፡1) ከራሱ ጋር እየተቃረነ አልነበረም። ሁለተኛ፥ የማቴዎስ

13 ዓውደ-ንባብ የሚያሳየው በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ የሚሰነዘረውን ተቃውሞና የማይቀርለት የሚመስለውን ሽንፈት እንጂ ዓለም-አቀፋዊ ድል አድራጊነትን አይደለም። የኋላ ኋላ ድል መገኘቱ ባያጠራጥርም፥ በመካከሉ ከተዘራው ዘር ብዙው ፍሬ አይሰጥም፤ ሰይጣን የማታለያ ዘሮችን የሚዘራ ሲሆን፥ መረቧ መልካም ከፉ ሳትል ሁሉንም ዓይነት ዓሦች ታግበሰብሳለች። በቤተ ክርስቲያን ታሪክም ሆነ በዘመናዊ ዘገባዎች ውስጥ የእግዚአብሔር መንግሥት «ዓለሙን ሁሉ እንዳሸነፈች» የሚገልጽ አሳብ ላገኝ አልችልም። የሕዝቡ ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ ስፍራ እያጣን ነው!

አይሁዶች ቅዱሳን መጻሕፍትን ስለሚያውቁ፥ ኢየሱስ የተጠቀመባቸውን ምሳሌዎች ተገንዝበዋል። እርሾ ክፉን ነገር (ዘፀ. 12፡14-20)፥ ታላቅ ዛፍ ደግሞ ታላቅ የሆነውን የዓለም መንግሥት ያመለክታል (ዳን. 4፡ 20-22፤ ሕዝ. 17፡22-24፤ 31፡3-9)። የሰናፍጭ ቅንጣት ትንሿ ተክል እንጂ ትልቅ ዛፍ ልታመርት አትችልም። መንግሥቱ በሐሰት ትምህርት ይበከልና (ገላ. 5፡1-9) ትንሿ ዘር («ታናሽ መንጋ» 12፡32) የሰይጣን ቤት ወደሚሆን ድርጅት ታድጋለች። (ወፎች ክፋውን ይወክላሉ- ማቴ. 13፡19።) ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ነኝ የምትለው ድርጅት ሁለቱንም ገለጻዎች ታሟላለች።

### 3. ስለ ደኅንነት የቀረበ ሥነ-መለኮታዊ ጥያቄ (13፡22-30)።

በዮሐንስ 9 እና 10 የተመዘገቡት ክስተቶች በቁጥር 21 እና 22 መካከል ቢቀመጡ ያስኬዳሉ። በዮሐንስ 10፡40-42 ኢየሱስ ይሁዳን ለቅቆ ከዮርዳኖስ ማዶ ወደ ቤሪያ እንደ ሄደ ልብ በል። ከዚያም ጌታችን ቀስ በቀስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዝ በሉቃስ 13፡22-17፡10 የተጠቀሱት ክስተቶች ተፈጸሙ።

ጻፎች ብዙ ጊዜ ስንት ሰው እንድሚድን የሚወያዩ ሲሆን፥ አንድ ሰው ኢየሱስ በጉዳዩ ላይ የራሱን አሳብ እንዲሰጥ ጠየቀው። ስለ ጲላጦስ እንደተነገው ጥያቄ ሁሉ፥ ኢየሱስ ይህንንም ጉዳይ የግል አድርገው መለሰው። ጥያቄው «ስንት ሰዎች ይድናሉ?» የሚል ሳይሆን «እኔ ድኚአለሁ ወይስ አልዳንሁም?» የሚል ነው። «በመጀመሪያ ይህንን አስተካክልና ሌሎች እንዲድኑ ለመርዳት ምን ማድረግ እንዳለብን በኋላ እንነጋገራለን» ብሎታል።

አንዳንድ ጊዜ ስለ ቅድመ-ውሳኔ፥ ምርጫና ሌሎችም አስቸጋሪ ዶክትሪኖች ለመሟገት ከሚፈልጉ የሬድዮ አድማጮቼ «ሥነ-

መለኮታዊ ደብዳቤዎች» ይደርሱኛል። ለጥያቄዎቻቸው መልስ በምሰጥበት ጊዜ በአብዛኛው ስለ ጸሎት ሕይወታቸው፥ ስለ ምስክርነታቸውና በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው ስለሚያበረክቱት አገልግሎት እጠይቃቸዋለሁ። ብዙውን ጊዜ መጻጻፉ በእነዚህ ጥያቄዎች ምክንያት ይደመደማል። ክርስቲያኖች ነን የሚሉ እጅግ በርካታ ሰዎች በእነዚህ ዋንኛ ዶክትሪኖች ላይ ለመወያየት ይፈልጋሉ፤ ዳሩ ግን ሰዎችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመማረክ በመሻት ተግባራዊ ሕይወት ለመምራት አይፈለጉም። ዲ. ኤል. ሙዲ፥ «ጌታ ሆይ፥ የተመረጡትን አድንና ከዚያ በኋላ ሌሎችን ምረጥ!» ሲሉ ጸልየዋል።

«ብዙዎች ሊገቡ ይፈልጋሉ፤ አይችሉምም» (ቁጥር 24)። ለምን? ምሳሌው ምክንያቱን የሚነግረን ሲሆን፥ በቀዳሚነት በዘመኑ በነበሩት አይሁዶች ላይ ያተኩራል። ይህም ሆኖ፥ ዛሬ ለሁላችንም የሚሆን ተግባራዊ ተዛምዶ አለው።

ኢየሱስ መንግሥቱን የእምነት አባቶችና ነቢያት በክብር እንደሚገኙበት ታላቅ ድግስ አድርጐ ገልጾአል (ቁጥር 28)። ዳሩ ግን ከተጋበዙት ሰዎች ምላሽ ለመስጠት የዘገዩት በጣም ብዙዎች ናቸው! በመሆኑም፥ ወደ ግብዣው ቦታ በሚደርሱበት ጊዜ ጊዜው በማለፉ በሩ ይቆለፍባቸዋል (14፡15–24፤ ማቴ. 22፡1–14 ተመልከት)።

ብዙ መዘግየት ለምን አስፈለጋቸው? ምሳሌው አያሌ ምክንያቶችን ይሰጣል። በመጀመሪያ ደረጃ፥ ደኅንነት ቀላል ነገር አይደለም። ኃጢአተኛው በጠባቡ ደጅ ሊገባና በዚያው መንገድ ሊራመድ ይገባዋል (ቁጥር 24፤ በተጨማሪ 9፡ ከ23 ጀምሮ ተመልከት)። የዓለሙ ሕዝብ የሚሄደው ወደ ጥፋት በሚወስደው በቀላሉ መንገድ ነው (ማቴ. 7፡13–14)፤ እናም ከብዙኃኑ ጋር ተቀላቅሎ መጓዝ ቀላል ይሆናል።

ሌላው የመዘግየታቸው ምክንያት የተሳሳተ የደኅንነት ዋስትና መያዛቸው ነው። ኢየሱስ በመካከላቸው የነበረ ከመሆኑም በላይ፥ አብረውት ተመግበው ደስ ተሰኝተው ነበር፤ ዳሩ ግን ከቶውንም በእርሱ አላመኑም። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ብዙ በሮችንና ዕድሎችን ቢሰጣቸውም አልተጠቀሙባቸውም (10፡13–16 ተመልከት)። እግዚአብሔር ታጋሽ ነው፤ ዳሩ ግን ይኸው ታጋሽ አምላክ እንኳ በሩን የሚዘጋበት ቀን ይመጣል።

ትዕቢትም ከፍተኛ ድርሻ ነበረው፤ ይኸውም በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸውን አለማዋረዳቸው ነው። በራሳቸው ዓይን የመጀመሪያዎች ቢሆኑም፤ በእግዚአብሔር ዓይን ግን የመጨረሻዎቹ ነበሩ– አሕዛብ ስፍራቸውን ይወስዱ ነበር! (ማቴ. 21፡43 ተመልከት)። የማያምኑ

አይሁዶች ከውጭ ተቀምጠው፥ «ርኩሳን አሕዛብ ውሾች» አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ በሚገኙበት በዓል ውስጥ ሲቀመጡ ይታይህ!

እነዚህ ሰዎች ከደኅንነት ርቀው የጠፉት ጥንታዊ ሃይማኖታቸው እንደሚያድናቸው በማመናቸው ነው፤ ኢየሱስ ግን እንደ በደለኞች እንጂ እንደ ጽድቅ አድራጊዎች አድርጎ አልተመለከታቸውም ነበር (ኢሳ. 64፡4፤ ቲቶ 1፡16)። ወግ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲገባ ከተፈለገ ወግን ከማክበር የበለጠ ነገር ያሻዋል።

ይሁንና፥ ዋነኛው ምክንያት የተሰጠው በራሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ይኸውም «አልወደዳችሁም» የሚለው ነው (ቁጥር 34)። ምንም እንኳ ቃሉ ወደ አእምሮአቸው ቢደርስ (ቁጥር 26) እና ልባቸው በታላቅ ሥራው ቢነካም፥ ልባቸው በመደንደኑ ምክንያት ለፈቃዱ ሊገዙ አልቻሉም ነበር። ይህ የመዘግየት የከፋ ውጤት ነው። ኃጢአተኞች ብዙ በዘገዩ መጠን ልባቸውም ይበልጥ እየደነደነ ይሄዳል። «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ» (ዕብ. 4፡7)።

የስፔይኑ የሙዚቃ ግጥም ደራሲና አቀናባሪ ማኑኤል ዲ ፎላ ለደብዳቤ ምላሽ ባለመስጠቱ የታወቀ ነበር። ይህ ሰው የጓደኛውን መሞት ሲሰማ፥ «ምንኛ የሚያሳዝን ነገር ነው! ከአምስት ዓመታት በፊት ለላከልኝ ደብዳቤ መልስ ሳልሰጠው ሞተ!» ብሏል።

ኃጢአተኞች እግዚአብሔር ወደ ድግሱ እንዲመጡ የሚያቀርብላቸውን ግብዣ ሳይቀበሉ ቢቀሩ የሚሞቱት ራሳቸው ናቸው። ከመንግሥቱ ደስታ ተገፍትረው ይወጡና በልቅሶና ጥርስ በማፏጨት ይቀጣሉ (ቁጥር 28)። ይህም ሰዎች በመዘግየታቸው ምን ያህል የሞኝነት ተግባር እንደፈጸሙ ተረድተው በጸጸት እንደሚርዱ የሚያሳይ መግለጫ ነው፤ የሚያሳዝነው ግን ተመልሰው ሊያስተካክሉት እስከማይችሉ ድረስ መዘግየታቸው ነው። ከሲኦል ሥቃዮች አንዱ የባከኑትን መልካም አጋጣሚዎች ማስታወሱ ይሆናል።

መልሱ ምንድን ነው? «በጠበበው በር ለመግባት ተጋደሉ» (ቁጥር 24)። «ተጋደሉ» የሚለው ቃል የተወሰደው ከስፖርት ሜዳ ሲሆን፥ ውድድሩን በድል ለመፈጸም የሚችለውን ሁሉ ጥረት የሚያደርገውን ሯጭ ይገልጻል። ሥቃይን የሚገልጸው የእንግሊዝኛ ቃል (agonize) ከዚሁ ቃል የተገኘ ነው። ዛሬ ሰዎች ለሩጫ የሚያደርጉትን ያህል ጥረት ለመንፈሳዊ ነገሮች ቢያደርጉ ምንኛ ባማረባቸው።

## 4. ስለ አደጋ የቀረበ የግል ጥያቄ (13፡31–35)።

ኢየሱስ የታላቁ ሄሮድስ ልጅ አንቲጳስ ሄሮድስ በሚገዛበት በቤሪያ ነበር። ፈሪሳውያን ኢየሱስን የሃይማኖት መሪዎች ሊጠብቁትና በመጨረሻም ሊያጠምዱት ወደሚችሉበት ወደ ይሁዳ እንዲመለስ ፈልገው ሊያስወጡት ሞከሩ።

ሄሮድስ በጌታችን አገልግሎት ግራ ተጋብቶ አንገቱን አስቆርጦ የገደለው መጥምቁ ዮሐንስ ከሞት የተነሣ መስሎት ፈራ (9፡7–9)። እንዲያውም በአንድ ወቅት ሄሮድስ ኢየሱስ ተአምር ሲሠራ ሊያይ ወድዶ ሊገናኘው ፈልጐ ነበር (23፡8)። በዚህ ጊዜ ግን ኢየሱስን ለመግደል መዛቱ የሄሮድስ ልብ እየደነደነ መምጣቱን ያሳየናል። ፈሪሳውያን የሰጡት ማስጠንቀቂያ ያለጥርጥር እውነት ነበር (ቁጥር 31፡)፤ ያለበለዚያ ኢየሱስ እንደዚያ አይመልስላቸውም ነበር።

«መለኮታዊ የጊዜ ሠሌዳ» ስለሚከተል እና ምንም ነገር እንደማይጐዳው ስለሚያውቅ ጌታችን ለአደጋ አልፈራም ነበር። በአብ መርሐ–ግብር መሠረት የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያደረገ ነበር (ዮሐ. 2፡4፤7፡30፤8፡20፤13፡1፤17፡1 ተመልከት)። የእግዚአብሔር ልጅ በፋሲካ ሰሞን በኢየሩሳሌም ከተማ እንደሚሰቀል ድሮ ከዘላለም የተወሰነ በመሆኑ (1ኛ ጴጥ. 1፡20፤ ራእ. 13፡8)፥ አንቲጳስ ሄሮድስም እንኳ የእግዚአብሔርን ዓላማ ሊያደናቅፍ አይችልም። የጌታችን ጠላቶች ካሰቡት ውጭ የጌታን ፈቃድ ለመፈጸም አገዛ ከማድረግ በቀር የጐዱት ነገር አልነበረም (የሐዋ. 2፡23፤3፡13–18)።

ኢየሱስ መልስ ሲሰጥ መጠነኛ «ፌዝ» ተጠቅሟል። ሄሮድስን አይሁዶች ከፍተኛ ግምት ከማይሰጡት ቀበሮ ጋር አወዳደረው (ነህ. 4፡3)። በብልጣብልጥነቱ የታወቀው ቀበሮ ለአታላዩ ሄሮድስ ተስማሚ መግለጫው ነበር። ኢየሱስ ሥራ ስለነበረበት ያንኑ ለመፈጸም ወሰነ። ኢየሱስ በብርሃን ሲመላለስ (ዮሐ. 11፡9–10፤9፡4)፥ ቀበሮዎች በጨለማ ውስጥ ተተራምሰዋል።

በተጨማሪም፥ ኢየሱስ ስለ ሕዝቡ የሚለው ነበረው፤ «ዳሩ ግን ነቢይ ከኢየሩሳሌም ውጭ ይጠፋ ዘንድ አይገባምና» (ቁጥር 33)። ይህ በሉቃስ 11፡47–51 ለጻፎችና ፈሪሳውያን ከተናገረው አሳብ ጋር ይዛመዳል። ሕዝቡ እግዚአብሔር ለድግሱ ያቀረበላቸውን የፍቅር ግብዣ አለመቀበል ብቻ ሳይሆን፥ ግብዣውን ያመጡላቸውን አገልጋዮች ሳይቀር ገድለዋል! (የሐዋ. 13፡27ን ተመልከት።)

ጌታችን በዙሪያው የነበረውን አለማመንና ዓመፅ ሲመለከት ልቡ በኃዘን ታመሰና ለአይሁድ ሕዝብ አሳዛኝ ሁኔታ አነባ። ይህ የቁጣ መግለጫ ሳይሆን የሥቃይ ኃዘን ነበር። ርኅሩኅ ልቡ ተሰበረ።

እንደ አይሁዳውያን በግብርና ለሚተዳደር ኅብረተሰብ የዶሮና ጫጩት ምሳሌ እንግዳ ሊሆን አይችልም [መዝ. (91)፡4] በብሉይ ኪዳን ውስጥ ክንፎች ከሚሉ ጥቅሶች አንዳንዶቹ በመገናኛው ድንኳን ወይም በመቅደሱ በቅድስተ ቅዱሳን የሚገኙትን የኪሩቤል ክንፎች ያመለክታሉ (ዘፀአ. 25፡20፤ ሩት 2፡12፤ መዝ. [36]፡7–8፤[61]፡4 ተመልከት)። ዶሮ የአደጋን መምጣት ስትመለከት ልጆቿን ትሰበስባለች። ፈሪሳውያን ኢየሱስ በአደጋ ውስጥ እንዳለ ነግረውታል፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን አደጋው ያንዣበበው በእነርሱው ላይ ነበር።

ይህ የኢየሱስ ለቅሶ ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ እንጂ ሊያስቆጡት ለሞከሩት ፈሪሳውያን ብቻ አልነበረም። ሕዝቡ ንስሐ ገብተው ይድኑ ዘንድ ብዙ በሮች ቢከፈቱላቸውም፥ ጥሪውን ለመቀበል አልፈለጉም ነበር። «ቤታችሁ» የሚለው የያዕቆብን «ቤተሰብ» («የእስራኤል ቤት») እና መቅደሱን («የእግዚአብሔር ቤት») ያመለክታል፤ ሁለቱም ወና ሆነው ይቀሩ ነበር። ከተማዪቱና መቅደሱ ፈራርሰው ሕዝቡ ተበታተነ፥

ይህም ሆኖ፥ ለእስራኤል የወደፊት ተስፋ አላት። መሢሕ ተመልሶ ሕዝቡ እርሱን ለይቶ የሚያውቅበትና የሚቀበልበት ቀን ይመጣል። በዚያን ጊዜም፥ «በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው።» ይላሉ [ቁጥር 35፤ መዝ. (118)፡26 ተመልከት]። ከሕዝቡ አንዳንዶቹ ወደ ኢየሩሳሌም በሚገባበት ጊዜ ይህንኑ ቃል የተናገሩ ቢሆንም (19፡38)፥ ትንቢታው ቃሉ የሚፈጸመው በክብር በሚመለስበት ጊዜ ነው (ማቴ. 24፡30–31፤ ዘካ. 12፡10፤ 14፤ ከ4 ጀምሮ)።

የእስራኤል ቤት ወና ሆኖ ቀርቶ ነበር። ንጉሥ ወይም ካህን፥ መቅደስ ወይም መሥዋዕት የላቸውም (ሆሴ 3፡4–5)። ይሁንና፥ ሕዝቡ እንዳልተጣለ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ያረጋግጣል (ሮሜ. 11፡ከ1 ጀምሮ)። የሰላሙ አለቃ (ኢሳ. 9፡6) በዳዊት ዙፋን ላይ እስኪቀመጥ ድረስ (ኢሳ. 11፡ከ1 ጀምሮ)፥ በምድር ላይ ሰላም ሊኖር አይችልም።

ለኢየሩሳሌም ሰላም ጸልዩ! [መዝ. (129)፡6]።

በጠበበው በር ለመግባት ተጋደሉ!

## አቤት፥ እርሱን መምሰል –
## ርኅሩኅ፥ በጭንቀት ላይ ላሉት እጁን
## የሚዘረጋ ቸር አምላክ!

**ኢየሱስ ክርስቶስ** ራሱን፥ «የሰው ልጅ» ሲል ጠርቷል። ለሁሉም ዓይነት ሰዎች... ለኃጢአተኞች... ለተጣሉት... የልብ ስብራት ላጠቃቸው... ለወንዶችና ለሴቶች... ለልጆች የርኅራኄ ወንዝ የሚፈልቅበት ልቡን ከፍቶላቸዋል። ሐኪሙ ሉቃስ ስለ ታላቁ ዶክተር ኢየሱስ ክርስቶስ የጻፈውን መልእክት በምታጠናበት ወቅት የእግዚአብሔርን ርኅራኄ ይበልጥ በመረዳት፥ አንተም ለሌሎች የላቀ የፍቅር አሳቢነት ለማሳየትና ሌሎችን በጭንቀታቸው ለመርዳት በእግዚአብሔር ርዳታ የምትችለውን ያህል ለማከናወን ትነሣሣለህ።

ዶ/ር ዌርዝቢ፥ ከዚህ ቀደም ከታየው ሁሉ በተለየ መንገድ እግዚአብሔር ሕዝቡን

## ርኅሩኅ ሁኑ

እያለ እንደሚጠራቸው ያምናሉ።

ዶ/ር ዋረን ደብልዩ. ዌርዝቢ ከሁሉም በላይ የሚታወቁት በደራሲነታቸው፥ በመጋቢነታቸውና በሬድዮ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በማቅረባቸው ነው። ለረዥም ዓመታት በሺካጎ የሙዲ መታሰቢያ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን፥ በቅርቡ ደግሞ «ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንመለስ» የተሰኘው ድርጅት ጄኔራል ዳይሬክተርና የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር በመሆን ሠርተዋል። ዶ/ር ዌርዝቢ በቪክተር ቡክስ የሚሰራጩትን የአዲስ ኪዳን ተከታታይ መጻሕፍት ጨምሮ፥ ከ100 በላይ መጻሕፍትን ጽፈዋል።